# bBebriti 2gna dereja mesenado temehrt bet afachewen beoromigna yefetu ye10gna kefel temariwoch beamarigna quanqua yemenager kihil yekefel weset ategebaber (□□□□ 2□ □□□ □□□□ □□□□□ □□ □□□□□ □□□□□ □□□ □1

*by* Melese Solomon

**Submission date:** 21-Sep-2023 02:51PM (UTC+0300)
**Submission ID:** 2172504867
**File name:** Melese_Solomon.pdf (1,015.35K)
**Word count:** 16241
**Character count:** 76511

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የድሕረ ምረቃ መረሐ ግብር


የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮምኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


**በብሪቲ 2ኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት አፋቸዉን በኦሮምኛ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ዉስጥ አተገባበር**


በ

መለሰ ሰለሞን

የጥናቱ አማካሪ

ጌታቸዉ አዱኛ (ዶ/ር)


መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በብሪቲ ሁለተኛና መሰናዶ ተምህረት ቤት አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድሕረ ምረቃ መረሐ ግብር

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥንት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት



አማካሪ

ጌታቸዉ አዱኛ (ዶ/ር)

በ

መለሰ ሰለሞን



መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


የሰንጠረዥ ማውጫ ........ III

**ምስጋና** ........ IV

**አጠቃሎ** ........ V

**ምዕራፍ አንድ** ........ 1

**1. መግቢያ** ........ 1

**1.1. የጥናቱ ዳራ** ........ 1

**1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት** ........ 2

**1.3. የጥናቱ አላማ** ........ 2

**1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ** ........ 3

**1.5. የጥናቱ ወሰን** ........ 3

**ምዕራፍ ሁለት** ........ 4

**2. ክለሳ ድርሳናት** ........ 4

2.1. የንግግር ክሂል ምንነት ........ 4

**2.2. የመናገር ክሂል የማስተማር አላማ** ........ 4

**2.3. የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት** ........ 6

2.4. የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አቀራረብ ........ 7

2.5. የንግግር ክሂል ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት ........ 8

**2.6. ንግግርን በምናስተምርበት ጊዜ የሚያጋጥሙን ችግሮች** ........ 9

**ምዕራፍ ሶስት** ........ 11

3. የጥናቱ ንድፍና ዘዴ ........ 11

3.1. የጥናቱ ንድፍ ........ 11

3.2. የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ ........ 11

3.2.1. የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ........ 11

3.2.2. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........ 11

3.2.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 11

3.3. የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያ ........ 11

3.3.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ ........ 11

3.3.2. የጽሁፍ መጠይቅ ........ 12

3.3.3. የቃል መጠይቅ ........ 12

3.4. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ........ 12

**ምዕራፍ አራት** ........ 13

4.የመረጃ ትንተና............................................................................................................13
4.1.1. ከምልከታ የተገኘ የመምህራን የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር ትንተና ....................................13
4.1.1.1. የመምህራን የንግግር ክሂልትምህርት የአቀራረብ ትግበራ ሁኔታ ትንተና........................................13
4.1.1.2. የተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ የመለማመድ ተግባራትን ............................15
4.1.1.3. የተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ........................................17
4.1.1.4. ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽ እንዲችሉ የመምህሩን ሚና............................................19
4.1.2. ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ የንግግር ክሂል አተገባበር የተማሪዎች ምላሽ...............................................20
4.1.2.1. መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት....................................20
4.1.2.2. የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ የላቸውን የማሪዎች ተሳትፎ በተመለከተ ..........................22
4.1.2.3. የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ያላቸውን የተማሪዎች ሀሳብን በነጻነት ............................24
የመግለጽ በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ትንተና...........................................................................24
4.1.3. ከቃለ መጠይቅ የተገኘ የንግግር ክሂል አተገባበር የመምህራን ምላሽ ...............................................26
4.1.3.1.የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ አቀራረብን በተመለከተ ከመምህራን.................................26
ቃለ መጠይቅ የተገኘ ትንተና.............................................................................................................26
4.1.3.2. የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ልምምድን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ..........................27
መጠይቅ የተገኘ ትንተና ...................................................................................................................27
4.1.3.3. የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ሀሳብን በነጻነት መግለጽን................................28
በተመለከተ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ትንተና...........................................................................28
4.2. የመረጃዎቹ ትንተና እና ማብራሪያ...........................................................................................29
4.2.1. የንግግር ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶችና ክንውኖች ...........................................................29
4.2.2. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ትግበራ.........................................................................30
5. ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ...............................................................................................32
5.1.ማጠቃለያ.............................................................................................................................32
5.2. መደምደምያ .........................................................................................................................32
5.3. የመፍትሄ ሀሳብ .....................................................................................................................33
ዋቢመጽሐፍት.............................................................................................................................34
አባሪዎች...................................................................................................................................36

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ሰንጠረዥ 1. የመምህሩ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ተግባራትን

በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ ውጤት የሚያመለክት መግለጫ........................................................13

ሰንጠረዥ 2. የተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልትምህርትን የመለማመድ

ተግባራትን የተመለከተ ትንተና..........................................................................................16

ሰንጠረዥ 3. የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ትምህርትንበክፍል ውስጥ ያላቸውን

ተሳትፎየተመለከተከምልከታየተገኘመግለጫ...............................................................................17

ሰንጠረዥ 4. የንግግር ክሂል ትምህርት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነፃነት መግለፅ እንዲችሉ

የመምህሩ ሚና የሚያሳይ መግለጫ...........................................................................................19

ሰንጠረዥ 5. የንግግር ክሂል ተግባራትን አቀራረብንየተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ

መስጫመግለጫ...............................................................................................................21

ሰንጠረዥ 6. የንግግር ክሂል ተግባራትን የተማሪዎችተሳትፎን የተመለከተየተማሪዎች

ምላሽ መስጫ መግለጫ.......................................................................................................23

ሰንጠረዥ 7. የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ሀሳብን በነፃነት

መግለፅን የተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ መስጫ መግለጫ...........................................................24

## ምስጋና

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ተጀምሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ ሰላምና ጤና ለሰጠኝና ዛሬ ላይ እንድደርስ ብርታቱን ለሰጠኝ ልዑል እግዚአብሄር ክብር ምስጋና ይግባው፡፡

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከጠናቀቅ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው በየጊዜው ገንቢ ሀሳቦችን በመስጠትና አስፈላጊ የሆኑ ምህሮችን በመለገስ ጥናቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ አብረውኝ ለነበሩ፤ እንዲውም የማማከር ሂደቱ የተሳለጠ እንዲሆን ያስቻሉት አማካሪዬ ጌታቸው አዱኛ (ዶ/ር) ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ የብሪቲ ሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት አስተዳደር፣ መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም በሃሳብ ለረዱኝ ውድ ጓደኞቼ ያለኝን ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

## አጠቃሎ

*ይህ ጥናት ዋና ትኩረቱ በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በኩዩ ወረዳ በብሪቲ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበርን ማጥናት ነው፡፡ ይህን ጥናት በሚገባ የታቀደለትን ግብ እንዲያስገኝ ለማስቻል መጠናዊና አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን የተሰበሰቡትን መረጃዎች በቁጥር ካስቀመጠ በኋላ በሚገባ በገለጻ መልክ አብራርቶዋል፡፡ የትምህርት ቤቱን አመራረጥ በወረዳው የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ስራ ላይ የሚገኘው አንድ ስለሆነ በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ተመርጧል፡፡የጥናቱ ተተኳሪ መምህራንም በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ተመጧል፡፡ ተማሪዎችም በአስረኛ ክፍል ውስጥ ከሚገኙ ሶስት ምድቦች በዕጣ ንሞና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በዚህ ሁኔታ የተፈለገውን መረጃ ለማግኘት የተመረጡትን ተተኳሪዎች መሰረት በማድረግ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅና የቃል መጠይቆች ተከናውነዋል፡፡ ይህም ማለት የክፍል ምልከታውን በክፍል ውስጥ በመገኘት የመምህርና የተማሪዎች የንግግር ቋንቋ አተገባበር ሂደታቸው የታየ ሲሆን የጽሁፍ መጠይቁን ደግሞ ለተማሪዎች በመስጠት እንዲሞሉ ከተደረገ በኋላ መምህራን ደግሞ የቃል መጠይቁን እንዲ መልሱ ተደርጓል፡፡ በምልከታ፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃል መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ትንተና ውጤት ለመረዳት እንደ ተቻለው መምህራን የእለቱን ትምህርት ከማቅረባቸው በፊት አላን በግልጽ በማናገር ሂደት ብዙ ጊዜ ጥሩ ቢሆኑም ግን የሚቀር ነገር እንዳለ ያሳያል፡፡ በክፍል ውስጥ የመማርማስተማር ሂደት ተማሪዎችን ያሳተፈ አለመሆኑ፤ መምህራን በንግግር ትምህርት ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ እንዲያድግ አለማድረጋቸው፤ ተማሪዎች ክርክር፣ ጭውውትና ውይይት እንዲያደርጉ አለማድረጋቸው፤ መምህራን ሁሉም ተማሪዎች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው አለማስቻላቸው፤ ሁሉም ተማሪዎች የንግግር ልምምድ እንዲያደርጉ አለማድረጋቸው፤ ተማሪዎች እርስ በርስ የመወያየት ባህል እንዲኖራቸው አለማድረግ፤ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገለጹ አለማበረታታቸው፤ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የግል፣ የቡድንና የጥንድ ስራዎችን እንዲሰሩ አለማስቻላቸው፤ ስዕሎች፣ ፎቶ ግራፎችና ቅርጻ ቅርጾችን በመጠቀም ተማሪዎች ንግግር እንዲያቀርቡ አለማድረጋቸው፤ ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎችን ለማበረታታት አለመሞከራቸው ለማረጋገጥ ተችሎዋል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡትን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት አላማን ግልጽ ማድረግ፣ ተማሪዎች የንግግር ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ፣ ሁሉንም ተማሪዎች እኩል ማሳተፍ፣ ተማሪዎች እርስ በርስ የመወያየት ባህሪ እንዲኖራቸው ማድረግ፣ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽ እንዲችሉ ማድረግ፣ ፎቶ ግራፎችና ስዕሎችን በመጠቀም ተማሪዎች ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ቢደረግ በማለት የመፍትሄ ሀሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት አላማ ተማሪዎች ስለ ቋንቋ ምንነትና መዋቅር እውቀት እንዲኖራቸዉ ማድረግ ብቻ ሳይሆን አራቱን የቋንቋ ክሂሎች በማዳበር በታላሚው ቋንቋ ተጠቃሚ እንዲሆኑና ችሎታቸውን በሚገባ እንዲያሳድጉ ማድረግ ነው፡፡ይህም ማለት ተማሪዎች ቋንቋን በሚማሩበት ወቅት የተለያዩ የቋንቋ ክሂሎችንም አብረው እያሳደጉ እንዲሄዱ ይረዳል፡፡እነዚህ የቋንቋ ክሂሎች ደግሞ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ናቸው፡፡የቋንቋ ትምህርትም እነዚህን ክሂሎች ለማዳበር እና ማህበራዊ መስተጋብርን ለማሳደግ ፋይዳው የጎላ ነው፡፡

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ አላማ ተማሪውታላሚውን የቋንቋ ስርአትና አጠቃቀም ወይም እውቀትና ክህሎት አውቆ በቋንቋው መግባባት እንዲችል ማድረግ ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት የሚጠበቀው ግብ በታላሚው ቋንቋ የማዳመጥ፣የመናገር፣የማንበብና የመፃፍ ክሂሎችን ማዳበር እንዲሁም የስነልሳንና የስነፅሁፍ መሰረታዊ እውቀትን ማስጨበጥ ነው (አብረሀም ፣2003)፡፡ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች እንደምናዳብር ያስረዳናል፡፡በዚህ ሂደት ዉስጥ ደግሞ መምህራን ትልቅ ሚና አላቸው፡፡

መምህራን የቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደትን የተሳካና ግቡን የመታ እንዲሆን የተለያዩ ክንዉኖችን ይተገብራሉ፡፡ክንዉኖቹም በአብዛኛው የሚያተኩሩት በይዘት መረጣ፣ በማስተማር ዘዴና ይዘቱን ለመተግበር የሚያስችሉ ክንውኖችን በማደራጀት ላይ ነው፡፡Littie wood (1981፣)፣ Widdowsen(1992)እና Kumara(2014) ይህንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩ የቋንቋ ማስተማር ሂደት ክንዉኖች ዉስጥ ምንና እንዴት እናስተምር የሚለው ጥያቄ ግንባር ቀደም ሲሆን፣ ይህም የይዘት መረጣና የማስተማርያ ስልት መወሰንን ይመለከታል፡፡ በተለይም ከይዘት መረጣ በኋላ የማስተማሪያ ስልትን መወሰን በጣም አስፈላጊ ነዉ፡፡ የማስተማሪያ ስልት ተብለውከሚጠቀሱት ዉስጥ አንዱ የንግግር ክሂልን ለመተግበር የሚያግዘው ተግባቦታዊ አቀራረብ ሲኖር ነዉ፡፡

የአንድ የቋንቋ መምህር ዋና ትኩረት ተማሪዎችን ስለቋንቋው መዋቅር ክፍሎች ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን በቋንቋው የተለያዩ ክሂሎችን በመገልገል ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን በመከወን ና ተገቢ የሆኑ ስልቶችን በመጠቀም ችሎታቸዉን እንዲያሳድጉ መርዳት መሆን አለበት (Byme 1976፣)፡፡ሀሳብን በንግግር በሚገልፅ ወቅት መታየት የሚገባቸዉና ከንግግር ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም ሀሳብን በትክክለኛ የአረፍተ ነገር አሰካክ

መግለፅና የተገለፀዉ ሀሳብ በንግግር ዉስጥ ከሚታየው አካላዊ እንቅስቃሴ ጋር የተዛመደናየተመጣጠነ መሆን አለበት (Byget 1987)፤ (Dedi 2017)፡፡

ንግግር በቋንቋ አማካኝነት ሀሳብን በቃል መግለፅ እንደሆነ የመስኩ ባለሙያዎች አረጋግጠዋል (Widdowson 1977፣48)፡፡ ሀሳብ በንግግር በሚገልፅበት ወቅት መታየት የሚገባቸዉና ከንግግር ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም ሀሳብን በትክክለኛየአረፍተ ነገር አሰካክ መግለፅና የሚገለፀው ሀሳብ በንግግሩ ወቅት ከሚታየዉ አካላዊ እንቅስቃሴ ጋር የተደጋገፈና የተጣጣመ መሆን አለበት የሚሉ ናቸው (Widdowson 1977:59-60)፡፡በክፍል ዉስጥ የንግግር ክሂል አተገባበርን በሚመለከት ከመምህር መር የመማር ማስተማር ዘዴ ይልቅ ቡድኖችን በተለያየ መልክ በማደራጀት የተለያዩ ተማሪዎች የተለያዩ ሀሳቦችን በማፍለቅ እንዲነጋገሩ ያደርጋል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን መምህሩ የሚከተለዉ መምህር መር የማስተማር ዘዴ አተገባበር ተማሪዎች ሀሳብን ለመረዳት ብዙ ጊዜያቸውን ያጠፋሉ(Kumara 2014)፡፡

Byget (1991) በበኩላቸ የክፍል ዉስጥ የንግግር ተግባራት ተማሪዎች ራሳቸውን የመግለፅ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ስለሆነ የቋንቋውን ትምህርት ዋነኛ አካል በመሆን በተገቢው መንገድ ሊሰጥ እንደሚገባ ገልፀዋል፡፡Byget(1987:viii) ሀሳባቸዉን እንደዚህ ይገልፃሉ ተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት በማዳበር በሚያደርጉት ንግግር እለታዊ ተግባሮቻቸዉን ማከናወን ይፈልጋሉ፡፡ በንግግራቸዉም ማንነታቸው ይለካል፣ በተግባቦቱም ጓደኛነት ሊመሰረቱ ወይም ሊያጡ ይችላሉ፡፡ስለዚህ ንግግር አመርቂ የሆነ ማህበራዊ ትብብር፣ ማህበራዊ ቦታ፣ ሙያዊ ከበሬታ....መመስረቻ መንገድ ከመሆኑም

በተጨማሪም ቋንቋን ለመማር በመሳሪያነት በማገልገል ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ይህም መናገርን የማስተማር ተገቢነት እሳቤ ያጎላል፡፡

የንግግር ክሂል በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባና ተማሪዎችን በማንኛዉም ተግባቦታዊ እንቅስቃሴያቸዉን ተማምነው ጥሩ የሆነ ማህበራዊ ግንኙነት የሚፈጥሩበት በመሆኑ በክፍል ዉስጥ ዘመናዊ ስልቶችን ተጠቅሞ ማስተማሩ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው(Byget 1987:viii)፡፡

ከላይ በተለያዩ የመስኩ ምሁራን እንደተገለፀው የመናገር ክሂል ማህበራዊ ግንኙነታቸዉን ለማከነወንና ዕለታዊ ክንዉኖቻቸዉን ለመተግበር ጉልህ ድርሻ የሚያበረክት ቢሆንም ክሂሉን ለማዳበር የሚያስፈልጉ ተግባራትን በማስተማርያ ስልቶችና መሳሪያዎች በማካተትም ሆነ በክፍል ዉስጥ አተገባበሩን በተመለከተ ትኩረት መስጠት እንዳለበት አስመልክተዋል፡፡ይህም ስለሆነ የመምህራን የመናገር ክሂል አቀራረብ ምን እንደሚመስል መፈተሽና መገምገም ያስፈልጋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የአማርኛ ቋንቋ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ከ5ኛ ክፍል ጀምሮ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጣል፡፡ ስለዚህ የቋንቋውን አገልግሎት ደረጃለማሳደግ የተማሪዎችን የማንበብ፣ የመፃፍ፣ ችሎታ ከማሳደግ በተጨማሪ ሀሳብ በንግግር የመግለፅ ችሎታን ለማሳደግ መጣር አስፈላጊ ነው፡፡የቋንቋ ትምህርት የክፍል ዉስጥ ልምድና ክንውኖችን ጨምሮ ሰዋሰውን፣ የማንበብን፣የመናገርን ክሂሎችን የሚያጠቃልል ነው፡፡ እነዚህ ክሂሎችና ክንውኖች በቋንቋ የመማር ማስተማር ዉስጥ ቢካተቱም ብዙዎች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በንግግር ሀሳባቸውን መግለፅ ያስቸግራቸዋል፡፡ ጥሩ የንግግር ችሎታም የላቸውም፡፡

አብዛኛዎቹ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ትኩረታቸው የተማሪ መፅሀፍ ላይ በሚገኘው የንግግር ክሂል መልመጃዎች እንጂ ለክፍል ዉስጥ የንግግር ክሂል አተገባበር እምብዛም ትኩረት እንደማይሰጡ በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ ጥናቶች ጠቅሰዋል፡፡ ከነዚህም ጥናቶች ዉስጥ (እጅጉ፣ 2003፣ አብረሀም፣ 2003፣ ከበደ፣ 2000) ይጠቀሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ጥናቶች የተጠኑበት ጊዜና የክፍል ደረጃ ከኔ ጥናት ይለያሉ፡፡ በተጨማሪም ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች በአፈ ፈት ተማሪዎች ላይ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ኢአፈ ፈት ተማሪዎችን ይመለከታል፡፡ ስለዚህ አጥኚው ለዚህ ጥናት መነሻ የሆነውበስራው አካባቢ ባገኘው ተሞክሮ ለመገንዘብ እንደቻለው ተማሪዎች በመማር ሂደት ዉስጥ በንግግር ክሂል ከሚያሳዩት ደካማ ግብረ መልስ መነሻ በማድረግና መምህራኑ በመማርያ መፅሀፍ ዉስጥ የሚገኙትን የንግግር ክሂል ማስተማርያ መልመጃዎችን ከሚያስተምሩበት ከባቢያዊ ሁኔታ ጋር በማዋሀድ በሚገባ መተግበር አለመተግበራቸዉን ለማወቅ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የሚከተሉትን መሰረታዊ የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ ይሞክራል፡፡

1. የ10ኛ ክፍል መምህራን በአማርኛ ክፍለ ጊዜ የንግግር ክሂልን እንዴት

   ይተገብራሉ?

2. መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ዉስጥ ሲተገብሩት የተማሪዎች

   ግብረ መልስ እንዴት ይገመገማል?

3. በንግግር ትምህርት ጊዜ የመምህራንና የተማሪዎች ንግግራዊ ተራክቦ እንዴት

   ይብራራል?

## 1.3. የጥናቱ ኣላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በኩዩ ወረዳ የብሪቲ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂል አተገባበር መፈተሽ ነው፡፡ጥናቱ ከዚህ አብይ አላማ በመነሳት የሚከተሉት ንዑሳን ኣላማዎች አሉት፤

1. መምህራን የንግግር ክሂል ትምህረትን በክፍል ዉስጥ እንዴት እንደሚተገበር

   መፈተሽ፡፡

2. የንግግር ክሂል ትምህርትን በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በሚተገበሩበት ወቅት

   የተማሪዎችን ግብረ መልስ መመርመር፡፡

3. የንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት የመምህራንና የተማሪዎችን ንግግራዊ ተራክቦ

   መገምገም፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

መምህራን የንግግር ክሂልን የክፍል ውስጥ አተገባበር ተረድተው የትምህርቱ መቃናት አስፈላጊውንሁሉክትትልእንዲያደርጉ ይህ ጥናት ያበረታታል፡፡ስለሆነም በክፍል ዉስጥ በሚኖረዉ የመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ በመምህርና በተማሪ እንዲሁም በተማሪና በተማሪ መካከል ጥሩ መስተጋብር እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተማሪዎች በራስ መተማመናቸው እንዲጨምርና ሀሳባቸውን በነፃነት መግለፅ እንዲችሉ ያስችላቸዋል፡፡ ስለዚህ ጥናቱ የሚከተሉ ዝርዝር ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂልን በሚተገብሩበት ጊዜ ለተማሪዎቻቸው እንዴት ድጋፍ እንደሚያደርጉ ይጠቁማል፡፡
2. መምህራንና ተማሪዎች የመናገር ክሂልን በክፍል ዉስጥና በማህበራዊ መስተጋብር ለማዳበር የሚያደርጉትን ጥረት በተሳለ ሁኔታ እንዲተገብሩ አቅጣጫ ያሳያቸዋል፡፡
3. በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ለሚያካሄዱ ሌሎች ተመራማሪዎች መነሻ በመሆን

   ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተሚካሄደው የ2015 ዓ.ም በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ኩዩ ወረዳ ብሪቲ 2ኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት ነው፡፡ጥናቱም ያተኮረው በ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ዉስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር ላይ ሲሆን መምህራንና ተማሪዎች የዚህ ጥናት ተተኳሪዎች ናቸው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

# 2. ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የንግግር ክሂል ምንነት

ንግግር የሰው ልጅ በቃል አማካኝነት ማህበራዊ ተግባቦትን ከሚደረግበት የቋንቋ ክሂሎች ዉስጥ አንዱ ነው፡፡ ንግግር ስሜት ያፈለቀውን፣ አይን የተመለከተውን ወይም ከንባብና ከማዳመጥ የተቀሰመውን ግብአት መነሻ በማድረግ ሀሳብን ስረአት ባለው መንገድ ለሌላ ወገን ለማስደመጥ መሞከር ነው፡፡ በማዳመጥ ሀሳብን መቀበል እንደሚቻል ሁሉ ለተደመጠው ምላሽ ለመስጠትና መልዕክት ለማስተላለፍ ደግሞ መናገር ያስፈልጋል፡፡ መናገር በተፈጥሮ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ከማዳመጥ ቀጥሎ ከቤተሰብ፣ ከአካባቢና ከትምህርት ቤት የሚለመድ ክሂል ነው፡፡

ንግግር ሲባል ብዙ ጊዜ የሚታሰበው ገፅ ለገፅ በመቀራረብ ወይም በተለያዩ ቦታዎች ሆኖ ንግግርን ማስተላለፍ በሚችሉ መሳሪያዎችን በመጠቀም ቃላዊ የሀሳብ ልዉዉጥ የሚከናወንበት ነው፡፡ ንግግር ወደ አድማጭ ሲደርስ ምስል ፈጥሮ መልእክትን ማስተላለፍ እንዲችል ቃላዊ ከሆነው መግባብያ በተጨማሪ በሌሎችም መንገዶችም ሀሳብ እንዲጎላ ማድረግ ይቻላል፡፡ እነዚህ የሀሳብ ማጉለያዎች በተናጋሪው የፊት ገፅታ ላይ የሚታዩ ሁኔታዎች፣ የእጅና የተለያዩ የአካል ክፍሎች እንቅስቃሴዎች መሆናቸውን (Widdowson 1992:60) ይገልፃሉ፡፡

ንግግር ሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚከናወን ተግባቦታዊ ሂደት ነው፡፡ በንግሩ ሂደት ተናጋሪውና አድማጭ ይሳተፋሉ፡፡ ከንዋኔውየሚካሄደውበየተራና ሚና በመለዋወጥ ነው፡፡ ተናጋሪ የነበረው አድማጭ፣ አድማጭ የነበረው ደግሞ ተናጋሪ ይሆናል፡፡ ንግግር እዉቀትን፣ ፍላጎትን፣ አመለካከትን፣ ግንዛቤን፣ ስሜትን፣ ወዘተ. ለሌላ ሰው መግለጫ ክሂል ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በንግግር ሲከናወን በንግግሩ ዉስጥ አምስት ክፍሎች ተጠቃለው ይገኛሉ፡፡ እነሱም መልእክቱን አፍላቂ የሚተላለፈው መልዕክት የሚተላለፍበት መንገድ ሊሆን ይችላል (Echeverria 1987:6-7)፡፡

Harmer (2001:269-271)እና Florez and Marry(1999:55) ስለ ሀሳባቸዉን ሲገልፅ ንግግር ማለት ስሜታችንና ፍላጎታችንን በቃላት አማካኝነት መግለፅ የሚያችል መልእክትን ማመንጨት ማገናዘብንና ማዉጠንጠንን የሚያጠቃልል፣ በተናጋሪና በአድማጭ መካከል የሚከናወን ተግባቦት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ንግግር ሀሳብ እንደ መጣ ማፍለቅ ሳይሆን ሰዉ የተመለከተዉን፣ ስሜት ያፈለቀዉን፣በንባብና በማዳመጥ ያገኘዉን ሀሳብ መነሻ በማድረግ በቋንቋ ድምፆች

አማካኝነት መልእክትን ለሌላ ወገን በስረአት ማስተላለፍ መቻል ሲሆን በማህበራዊ ህይወት ዉስጥም የጎላ ሚና ይጫወታል(Celce-muricia & Oishtain 2000)፡፡

ንግግር እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ የመግባቢያ መንገድ ነው፡፡ በመሆኑም ሰዎች ከመሰሎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የመግባባት ሂደት መልእክታቸዉን በሚያስተላልፉበት ጊዜ ስረአትን ጠብቀው በብቃትና በጥራት ሊገለገልበት ይገባል በማለት (ተስፋዬ1981) ይገልፃሉ፡፡

ማረዉ (1998:139) እንደሚሉት የመናገር ክሂል ሊዳብር የሚችለው ህጎችን በማስተማር ወይም በመናገር ሳይሆን እንደ ማንኛዉም ክሂል በተግባራዊ ተሳትፎ ብቻ ነው፡፡ ተማሪዎች እየፃፉ ክሂላቸዉን እንደሚያዳብሩ ሁሉ እየተናገሩም የመናገር ክሂላቸዉን ማዳበር አለባቸው፡፡

# 2.2. የመናገር ክሂል የማስተማር አላማ

የመናገር ክሂል ማስተማር አላማ ተማሪዎችን በቋንቋው ጥሩ ተናጋሪ ማድረግ ነው፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች ያለምንም ፍረሀትና ጭንቀት በማንኛዉም ቦታ በምክንያትና ዉጤት ላይ የተመሰረቱ ማንኛቸዉም ንግግር በነፃነትና በግልፅነት ሀሳባቸዉን የመግለፅ ችሎታንም ያጠቃልላል፡፡ ይህንንም ለማሳካት እጅግ በጣም ብዙ ድካም የሚጠይቅ ሲሆን ተማሪዎች ወደ መድረክ እንዲወጡና የተሰጣቸውን ተግባራትን በትክክል እንዲያቀርቡ ለማድረግ ወይም በቋንቋ ተጠቅመው ነፃ ሀሳባቸዉን እንዲገልፁ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በድሉ (2007) ሲገልፁ በሀገራችን አብዛኞቹ ተማሪዎች የከፍተኛ ሑለተኛ ደረጃ ትምህርታቸዉን የሚያጠናቅቁት ጥሩ የንግግር ችሎታ ሳያዳብሩ ነው፡፡ በመሆኑም ከትምህርት ቤት በኋላ ባለውህይወታቸው ያለምንም ችግር ሀሳባቸዉን በንግግር ለመግለፅ ይቸገራሉ፡፡ በራስ ያለመተማመን፤ መልዕክትና ዉጤት አቀናጅቶ ያለማቅረብና የቋንቋዉን ስረአት ያለመጠበቅ ከሚያጋጥማቸው ችግሮች ዉስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የንግግር ክሂልን በክፍል ዉስጥ የማስተማር ዋና አላማም እነዚህን ንውሳን ክሂሎች በማዳበር ተማሪዎች ጥሩ የንግግር ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው፡፡

Byget (1987:8) ሀሳባቸዉን ሲገልጹ የመናገር ክሂል ትምህርት ከዚህ በታች የተጠቀሱት አላማዎች እንዳሉ ይጠቅሳሉ፡፡

- **የቋንቋዉን ድምፀ ልሳናዊ ባህሪያት አዉቀዉ አድማጭ ሊረዳ በሚችሉበት መንገድ መጠቀም እንዲችሉ፡-** የመናገር ክሂል ትምህርትን በሚከናወንበት ጊዜ አላማዉን ከግብ ለማድረስ ተማሪዎች የቋንቋውን ድምጸ ልሳናዊ ባህሪ አውቀው እንዲጠቀሙ ማስቻል ነው፡፡ይህም ማለት ተማሪዎቹ የቋንቋዉን የቃላት አጠቃቀም፣ የመጥበቅና መላላት እንዲሁም መዋቅሩን አውቀው እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው፡፡

**በንግግር ሂደት ሀሳብን በቅደም ተከተል አዋቅረዉ ማፍለቅ እንዲችሉ፡-**የመናገር ክሂል ትምህርት አላማ ተማሪዎች ሀሳብን በቅደም ተከተል በማዋቀር ማፍለቅ እነዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ይህም ሲባል ተማሪዎች በንግግር ትምህርት ጊዜ ንግግርን ለማቅረብ ሀሳባቸውን በሚገባ በማዋቀር ቅደምተከተላቸውን ይዘው ማቅረብ እነዲችሉ ማስቻል ነው፡፡

- **መስተጋብራዊ በሆነ ተግባቦት ሂደቶች መሳተፍ እንዲችሉ፡-**የመናገር ክሂል ትምህርት አላማ ተማሪዎች መስተጋብራዊ የሆኑ ተግባቦቶችን መሳተፍ እዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ተማሪዎች የመናገር ክሂልን ከግብ ለማድረስ በክፍል ዉስጥ መስተጋብራዊ የሆነ የተግባቦት ሂደቶችን መሳተፍ እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡
- **በዉይይት ሂደት የተደረሰባቸዉን ስምምነቶችንና ወደ ሚዲያዎች በቃል መዝግበዉ ማቅረብ እንዲችሉ፡-** የመናገር ክሂል ትምህርት አላማ ተማሪዎች የመወያየት ሂደት እንዲኖር ወደ ስምምነት መድረስ አንዲችሉ ማስቻልና ስምምነታቸውን ደግሞ መዝግበው በቃል ማቅረብ እነዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ይህም ተማሪዎች የተወያዩበትንና ወደ ስምምነት የደርሱበትን በመመዝገብ ለተለያዩ ሚዲያዎች ማቅረብ እንዲ ችሉ ማስቻል ነው፡፡

Nunan (1991:32) እንደሚገልፁት የአፍልቆት ክሂል የሆነዉን የመናገር ክሂልን የማስተማር አላማ የቋንቋ ፍሰትን ወደሚፈለገዉ ደረጃ ማድረስ ቢሆንም ስኬታማ ቃላዊ ተግባቦት የሚከተሉትን ክሂሎችን እንደሚያሳድግ ይጠቅሳል፡፡

- **የቋንቋዉን ስነ ድምፃዊ ባህሪ የመናገር(የማንበብ) ችሎታ፡-**ሰዎች የንግግር ትምህረትን በሚተገበሩበት ሰአት የቋንቋዉን ስነድምጻዊ ባህሪ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ይህም ሲባል ተማሪዎች የንግግር ትምህረትን በተግባር በሚከዉኑበት ጊዜ የቋንቋዉን ስነ ድምጻዊ ባህሪ የመናገር ችሎታ ሊያዳብሩ ይገባል፡፡የቋንቋ ስነድምጻዊ የመናገር ችሎታዎች ፡-ለምሳሌ፣ ቅላጼ፣ የመጥበቅነ መላላት፣ ምት ስረአቶችን ማወቅ አለባቸው፡፡
- **ተቀባይነት ያለዉ የቋንቋ ፍሰት ችሎታ፡-** አንድ ሰው የመናገር ክሂል ትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ ተቀባይነት ያለው የቋንቋ ፍሰት ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች የመናገር ትምህርትን በክፍል ዉስጥ በሚተገብሩበት ወቅት ተቀባይነት ያለው የቋንቋ ፍሰት ችሎታ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች ስኬታማ ቃላዊ ተግባቦት ለማድረግ የቋንቋውን ቅደም ተከተላዊ ሂደት በሚገባ ማወቅ አለባቸው፡፡
- **የዕለታዊ ተግባራትና የሰላምታ ልዉዉጥ ግንኙነት ክሂል፡-**ሰው የመናገር ክሂልን ለማሳደግ የተለያዩ ዕለታዊ ተግባራትንና የሰላምታ ልዉዉጦችን ያከናዉናል፡፡ተማሪዎች የመናገር ትምህርትን ተግባር በክፍል ዉስጥ በሚያከናዉኑበት ወቅት የእለታዊ ተግባራትና እርስበርስ የሰላምታ ልዉዉጥ ግንኙነቶችንም እያሳደጉ ይሄዳሉ፡፡ይህም ማለት እለታዊ ተግባርን ና የሰላምታ ልዉዉጣቸውን እነዴት ማከናወን እነዳለባቸው ያውቁበታል፡፡
- **ተራ ጠብቆ የመናገር ችሎታ ፡-**አንድ ሰው የተለያዩ ሀሳቦችን በሚናገርበት ጊዜ ተራጠብቆና የሰውን ጊዜና መብት ሳይጋፋ መሆን አለበት፡፡ተማሪዎችም የመናገር ትምህርት ክፍለ ጊዜ ላይ የንግግር ተግባርን ሲተገብሩ የሌላዉን ተማሪ ተራ በማይሻማ ሁኔታ የራሳቸውን ሀሳብ በተራቸው የመናገር ችሎታ እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፡፡
- **መስተጋብራዊ በሆነ የተግባቦት ሂደቶች የመሳተፍ ችሎታ፡-**አንድ ሰው ሀሳቡን በሚገባ ለመግለጽ ና ለሰው ለማድረስ መስተጋብራዊ ተግባቦት ሊኖረው ይገባል፡፡ስለዚህ ተማሪዎች የመናገር ትምህርት ተግባራትን

በሚተገብሩት ጊዜ ለሁሉም ሰው መስተጋብራዊ በሆነ የተግባቦት ሂደትን በተከተለ የመሳተፍ ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ተማሪዎች ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር ጥሩ የሆነ መስተጋብር ሊፈጥሩ ይገባል ማለት ነው፡፡

- **መልዕክትን የመቀበልና የመረዳት ክሂል፡-** ሰው ንግግር በሚደረግበት ጊዜ መልዕክትን የመቀበል ና የመረዳት ክሂል ሊኖረው ይገባል፡፡ይህም ማለት ተማሪ የመናገር ክሂል ትምህርትን በሚተገብርበት ጊዜ የሚተላለፍለትን ወይም እራሱ የሚያስተላልፈዉን መልዕክት የመቀበል ና የመረዳት ችሎታን ሊያዳብር ይገባል፡፡
- **የሀሳብ መሟያ ዘዴዎችን በአግባቡ የመጠቀም ችሎታ፡-**አነድ ሰው ንግግር በሚያደርበት ጊዜ የሀሳብ ማሟያ ዘዴዎችን በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ይህም ተማሪዎች የመናገር ክሂል ተግባርን በሚየከናዉኑበት ጊዜ የተለያዩ የሀሳብ ማሟያ ዘዴዎችን በሚገባ አዉቀው የመጠቀም ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

Bayget (1987:3) እንደ ተናገሩት በታላሚዉ ቋንቋ ለመግባባት የቋንቋዉን የቃላት አደረጃጀትና የሰዋሰው መዋቅሩን ማወቅ ጠቃሚ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ደግሞ በቋንቋዉ ለመልገል የሚያበቃ ክሂል ያስፈልጋል በማለት ገልፀዋል፡፡

## 2.3. የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት

የመናገር ክሂልን መማርና ማስተማር የሰዎችን የዕለት ከዕለት ህይወታቸዉን ቀለል አድርገው ኢንዲመሩና በቀላሉ መግባባት እንዲችሉ፣ የተለያዩ ጠቃሚ መረጃዎችን ማግኘት እንዲችሉ፣ የአነጋገር ስልታቸዉን ወደ መደበኛነት በማሳደግ ከሰዎች ጋር በቀላሉ መግባባት እንዲችሉና የተሰማቸዉን ወይም የግል አስተያየታቸዉን ለሀሳባቸ በሚመጣጠን ቋንቋ መግለጽ እንዲችሉ የመናገር ክሂልን መማርም ሆነ ማስተማር አስፈላጊ እንደ ሆነ **መረዳት ይቻላል፡፡**

የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊነት ተማሪዎች ሀሳባቸዉን ያለምንም መደናቀፍና መደናገር በንግግር ማስተላለፍ እንዲችሉ የሚያደርጋቸዉን እዉቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ነው፡፡ የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ቋንቋዉን በምን አይነት ሁኔታ እንደሚጠበቅ እዉቀትና ክሂሎት ማግኘት የሚቻለው በንግግር ክሂል ትምህርት ነው፡፡ቋንቋው ህብረተሰቡ በሚጠቀምበት መልኩ በክፍል ዉስጥም ሆነ በከፍል ዉጪ እንዲጠቀሙበት ለማስቻል የንግግር ክሂል ትምህርት አስፈላጊ ነው (Mac Donough and Shaw 1994:154)፡፡

Harmer (1991:15) በበኩላቸዉ ስለ ንግግር ትምህርት ሲገልጹ የንግግር ክሂልን ማስተማር አስፈላጊነቱ በሚከተሉት ነጥቦች ይገልፁታል፡፡

- የንግራቸዉን ፍሰት ጠብቀዉ ሀሳባቸዉን እንዲገልጹ፣
- ተግባቦታዊ ችሎታ እንዲዳብር፣
- ግላዊ አመለካከታቸዉን በንግግር ነጻ ሆነዉ እንዲገለጹ፣
- የቋንቋዉን ሰዋሰዋዊ ህግ ባግባቡ እነዲጠቀሙና እንዲያዉቁ፣
- ሀሳብን በተጠይቃዊ ቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ/ማስቀመጥን እንዲለማመዱ፣
- የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት ጥያቄ የመጠየቅ ክሂላቸዉን እንዲዳብር ለማስቻል፣
- የአነጋገር ስልታቸዉ ከኢ መደበኛ ወደ መደበኛ የአነጋገር ስልት እነዲመጣ፣
- በተለያዩ ቦታዎች ለሚነሱ ሃሳቦች የተለያዩ መከራከርያ ነጥቦችንና አስተያየቶችን በማስረጃ አስደግፈዉ ማቅረብ እንዲችሉ፡፡
- የተለያዩ ቃላትን በተገቢዉ ቦታና ጊዜ መጠቀም እነዲችሉ፣
- የትክክለኛነትና የአንደበተ-ርዕቱነት ችሎታቸዉ ከፍ እንዲል ለማድረግ የመናገር ክሂልን መማር አስፈላጊ ነዉ በማለት ገልጸዉታል፡፡

Brum (1984) እና Alumettu (2018) ተማሪዎች የንግግር ክሂልን ሲለማመዱ አንደበተ-ርቱነታቸዉን በአግባቡ እያሻሻሉ ይዳሉ:: በልምምዱ ወቅትም በየመሀሉ ምን ልናገር ብሎ አያቆምም ወይም እንዴት እራሱን መግለፅ እንዳለበት አይቸግረዉም:: ይህ አንደበተ-ርቱነት መሰረት የሚያደርገውየቋንቋው የቃላት አገባብ ዘዴዎችን በደንብ መጠቀም በቋንቋው መግባባት መቻልን ያዳብራል:: በመሆኑም የአንድ ተማሪ አንበተርቱነት የሚለካው ቋንቋን ቶሎ በመናገር፣ የቋንቋው የቃላት አሰካክ፣ የቋንቋዉን ሂደት የመቆጣጠር ብቃትና የቋንቋ ሰዋሰዋዊ አገባብን በአግባቡ መጠቀም ሲችል ነው:: በተጨማሪም መምህሩ አንደበተ-ርቱነትን ለማሳደግ በልምምድ ወቅት የተለያዩ መልመጃዎችን በትኩረት ሊሰጣቸዉ ይገባል በማለት ገልፀዋል::

## 2.4. የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አቀራረብ

የንግግር ክሂል አቀራረብ የሚወሰነው ተማሪው የቋንቋውን ንግግር በሚማርበት አላማ ነው(Annsnow 1991):: ተማሪው ቋንቋውን የሚማርበት አላማ በሶስት ጉዳዮች ሊወሰንይችላል:: በተማሪው በራሱ ፍላጎት፣ በሀገሪቱ የቋንቋ ትምህርት ፖሊሲና በቋንቋው ስረአተ ትምህርት ይወሰናል:: እነዚህ ሁኔታዎች ወሳኝ ቢሆኑም ከቋንቋ ትምህርት እሳቤ አንጻር በርከት ያሉ የቋንቋ ትምህርት የማስተማር አቀራረቦች በየጊዜው ሲወሱ ቆይተዋል::ከመምህር ተኮር እስከ ተማሪ ተኮር የቋንቋውን ህግጋት ከማጥናት ጀምሮ እስከ ቋንቋው ተግባቦታዊ ተግባራት ስራ ላይ እንድውል ተደርገዋል::

Rechards(1994) እና Benter(2015) እንደገለጹት የንግግር ክሂል አቀራረብ ተማሪዎች በቋንቋ ተጠቅመው ልዩ ልዩ ማህበራዊ አውዶች ውስጥ ሀሳባቸውን ለማስተላለፍ ይረዳቸው ዘንድ በቂ ልምድ ይሰጣቸዋል:: በተጨማሪም የተማሪዎች የንግግር ችሎታ እንዲጨምር፣ በክፍል ውስጥ ያላቸው የተነሳሽነት ብቃታቸው እንዲያድግና የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን እንዲያከናውኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው::

የንግግር ክሂል አቀራረብ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ አብዛኛውን ጊዜ ግልጋሎታዊም ሆነ ስነ-ልሳናዊ አላማው ከተማሪው ፍላጎትና ችሎታ አኳያ ይለያያል:: ተግባሩም የሚከናወነው በጥንድ ወይም በቡድን ሀሳብን መረዳት እንዲችል እንዲወያዩ፣እንዲከራከሩ ወዘተ.. የሚረዳ ነው::ይህም የንግግር ክሂልን ለማስተማር በከፍተኛ ደረጃ ሁኔታዎችን ያመቻቻል በማለት Rechards (1994) ያስረዳል::

Brown &Yule.(1983) እንደገለጹት አንድ የቋንቋ መምህር ንግግርን ከማህበራዊና ተግባራዊ ማነቃቂያ ጋር አያይዞ ማስተማር ተገቢ ነው:: ተግባራዊ ንግግርን ስናስተምር ተማሪዎች የመረጃ ልውውጥ እንዲያደርጉና እዚያው ክፍል ውስጥ ሊተገበሩ የሚችሉትን ስራዎችን ማከናወን ይቻላል:: በተጨማሪም ተማሪዎች ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እንዴት አድርገው እንደሚመሰርቱ ማስተማር፤ በክፍል ውስጥም በምን መልኩ እንደሚያከናውኑት ማስተማር፤ ከቤተሰቦቻቸውና ከጓደኞቻቸው ጋር በውይይት መልክ እንዲተገብሩ ማድረግ ይገባል::በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ አራቱን የቋንቋ ክሂሎችን መጠቀም የመምህሩና የተማሪው ተግባር ነው:: በተጨማሪም መምህሩ የተለያዩአዳዲስ መረጃዎችን በመጠቀምና በተቻለ መጠን በታላሚው ቋንቋ የሚቀርበውን ተግባር ግልፅና በማያሻማ መልኩ ማቅረብ አለበት:: በዚህ መልኩ ተግባራዊ ከሆን ተማሪዎች አዳምጦ መገንዘብና መናገር ይችላል Byrme (1987)::

Grant (1989) ስለ ንግግር ትምህርት አቀራረብ ሲገልጹ የቋንቋ ተማሪዎች የንግግር ችሎታ ከፍ ያደርጋል ተብሎ የተሰጠውን ትምህርት ከተማሩ በኋላተማሪዎች ሓሳባቸውን መግለጽ የማይችሉ ሆነው ይገኛሉ:: ይህ የሚሆንበት ምክንያት የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረቡ መምህሩን እንጂ ተማሪውን ያማከለ ስላልነበረ ነው:: ተማሪው በሰኮንድ ለሚቆጠሩ ጊዜያት እንኳ ቢሆን ለመናገር እድል ሳያገኝ መምህሩ ብቻ ተናግሮ ጊዜው ይጠናቀቃል:: ከዚህ በኋላ ተማሪው የንግግር ችሎታው ሳይዳብር ይቀራል፤ ካሉ በኋላ ይህንን ሁኔታ ለማስወገድ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ መለወጥ ይኖርበታል ይላሉ::

የንግግር ክሂል ትምህርት ለማስተማር እንደዝግጅቱ ሁሉ አቀራረብም ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነው። ስለዚህ ንግግርን ለማስተማር አላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተለውን የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎችን መጠቀም አስፈላጊ ነው።(Byme 1976: 3-4)

**1.አቀራረብ**

በዚህ ወቅት መምህሩ እንደ መረጃ ተቀባይ ሆኖ መሆን አለበት። መምህሩየተለያዩ አዳዲስ መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀምና በተቻለ መጠን በታላሚው ቋንቋ የሚቀርበው ተግባር ግልፅና በማይረሳ መልኩ ማቅረብ አለበት። በዚህ ደረጃ የንግግር ትምህርቱ በምልልስ መልክ ወይም በንባብ ሊቀርብ ይችላል።

### 2.ልምምድ

በልምምድ ወቅት አብዛኛውን ተግባር የሚያከናውኑት ተማሪዎች ናቸው። Byme (1986:34-52) እንደሚገልፁት ይህ ደረጃ አስቀድሞ በቀረበው የትምህርት ዐውድ መሠረት በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸውን ለማዳበር የሚለማመዱበት ነው።

### 3.አፍልቆት

በዚህ ደረጃ ማንኛውም የመናገር ዕድል ለተማሪዎች በመስጠት ቋንቋውን በራሳቸው እንዲጠቀሙበት (በነፃነት እንዲገልፁ) ማድረግ ነው። በአፍልቆት ደረጃ ዋናው ትኩረት ተማሪዎች በቀላሉና በነፃነት የሚግባቡትን ዐውድ መፍጠር እንዲሁም በጋራ የሚሰሩትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

## 2.5. የንግግር ክሂል ለማስተማር የሚረዱ ተግባራት

Harmer(2007) እና Shafaat(2018) እንደገለጹት ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንደ የሆነውን የንግግር ክሂልን የማጎልበት የክፍል ውስጥ የተማሪዎች ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡መምህሩ ተማሪዎችን ሊያሳትፍ የሚችለ የንግግር ክሂል ተግባራትን ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ እነዚህ የንግግር ክሂል ተግባራት ሲዘጋጁ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፍ ቢሆን ይመረጣል፡፡ይህም የተማሪዎችን በራስ የመተማመን ስሜት ይጨምራል፡፡ ተግባራቱም የመረጃ ክፍተት ተግባራት፤ አቅጣጫን ማሳየት፣የስዕሎችን ልዩነት መግልፅ፣በሰንጠረዥ መልክ የቀረቡ መረጃዎችን ማሟላት ሊይ ስለሚመሰረት የውስብስብነትበህሪይ አይታይበትም በማለት (Harmer2007)ገልጸዋል፡፡

በዘመነኛው የቋንቋ ትምህርት የተማሪ መራሽየትምህርት አቀራረብ ጠቀሜታ እንዳለው በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡በዚህም የተማሪዎቹን የግልም ሆነ የቡድን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ የጥንድናየቡድን ተግባራትን የሚጠይቁ መለማመጃዎችን ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡በንግግር የትምህርት አቀራረብ በውጤታማነታቸው ከሚጠቀሱ ልዩ ልዩየንግግር ማስተማሪያ ዘዴዎች (ልዩ ልዩ ተግባቦታዊ ክንውኖች) መካከልከዚህ በታች ያሉት ይገኙባቸዋል፡፡

ሀ. **ወደ ስምምነት መድረስ**፡-ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቡድን ተነገግረው የሀሳብ ልውውጥ ካደረጉ በኋላ ለእያንዳዳቸው ባፈለቁት ሃሳብ በመነጋገር የጋራ መግባባት ላይ የሚደርሱበት ስልት ነው፡፡በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ለሚየነሷቸው ሀሳቦች የጋራ መግባባት ላይ በሚደርሱበት ወቅት የንግግር ችሎታ ዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

ለ. **ችግር ፈቺነት**፡-ተማሪዎች በዉስጣቸው ያለውን ሀሳብ በማፍለቅ ለችግሮቻቸው መፍትሄ እንዲ ሰጡ የሚያደርግ ነው፡፡ይህም ሲባል በማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱትን ማንኛውንም ችግሮች ለመፍታት ተማሪዎች እርስበርስ ሀሳብ እንዲለዋወጡና በራስ መተማመን እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ Bygate.(1987) ሲገልጹ ተማሪዎች ችግሮችን ከሀሳባቸው አፍልቀው የችግሮችን ሁኔታዎች በቡድን የሚመራመሩበት ስልት ነው፡፡እንዲሁም ተማሪዎች የተወሰኑ ችግሮችን በማንሳት የችግሩን መፍትሄ ለመስጠት የሚሞክሩበት ሂደት ነው፡፡በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥያለትን ችግሮች በማንሳት የወደፊቱን እንዲተነብዩና የሚያመጣውንችግርእንዲያስቀምጡ፣ እርስ በርስ እንዲወያዩና አንድ ሀሳብ ላይ እንዲደርሱ ያደርጋቸዋል፡፡

ሐ.**ራስን መግለጽ**፡-በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች ስለራሳቸውና ስለታሪካቸው እንዲሁም ስለማንነታቸው በቋንቋ አማካኝነት በንግግር ለጓደኞቻቸው የሚገልጹበት ስልት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ተማሪዎች ስለ ራሳቸው በሚናገሩበት ወቅት የመናገር ክሂላቸውንም ያሳድጋሉ፡፡

መ. **ምስለትና የሚና ጨዋታ**፡-ሚና ጫወታ ተማሪዎች በራሳቸው ገጠመኝ ይሁን ወይም በሌሎች በሚታየው ነባራዊ ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ የሚያከናውኑት ተግባር ሲሆን የተለያዩ ክርክሮችንና ውይይቶችን ለማከናወን አስፈላጊ ነው፡፡

ሠ.**ታሪክን ማዋቀር**:-ተማሪዎችከዚህቀደምየሰሙትንታሪክወይምእራሳቸውየፈጠሪትንበማዋቀርለክፍልጓደኞቻቸውየሚያቀርቡበትስልትነው፡፡ይህ ምተማርዎቹታሪክንበሚገባማዋቀርናበክፍልውስጥእነዲያቀርቡይረዳቸዋል፡፡

Harmer (2007) ሲገልጹ ተማሪዎች ቀደም ሲል የሰሙትን ታሪክ ወይም በራሳቸው የፈጠሩትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ የሚያግዝ ስልት ነው፡፡ስልቱም

የተማሪዎችን የመፍጠር ችሎታን ያዳብራል፡፡እንዲሁም ተማሪዎች ሀሳባቸውንመግቢያ፤ሀተታና መደምደሚያን በያዘ ቅርጽ በማቅረብ እንዲለማመዱና የታሪኩን ባህሪያትና መቼት አስመስለው እንዲያቀርቡ ይረዳል፡፡ሂደቱንም እንደሚከተለው ጠቅሰዋል፡፡

ሰ.**ውይይት**:-ተማሪዎች በቡድን በአንድ ጉዳይ ላይ በጋራ እንዲነጋገሩና አንድ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ የሚደረግበት ስልት ነው፡፡ ይህም ሲባል ተማሪዎች አንድን ጉዳይ በመውሰድ በጉዳዩ ላይ ሀሳብ በመለዋወጥ መፍትሄ ላይ ለመድረስ የሚደረግ ሂደት ነው፡፡

ረ. **ክርክር**:-ተማሪዎች በአንድ ሀሳብ ላይ የተለያዩ ልዩነቶችን (አቋም) በመያዝ በቡድን እርስ በርስ በመከራከርና የሀሳብ ልውውጥ በማድረግ ወደ አንድ ድምዳሜ የሚደርሱበት ስልት ነው፡፡ በዚህ ወቅት ተማሪዎች በቡዷን በመሆን ከተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶች በመነሳት የተለያዩ ዕዉቀቶችን የሚያገኙበትና የንግግር ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ነው፡፡

## 2.6. ንግግርን በምናስተምርበት ጊዜ የሚያጋጥሙን ችግሮች

ንግግርን በምናስተምርበት ጊዜ ከሂሉን በሚገባ ለማስተማርና ተማሪ በሚገባ ክሉን እንዲተገብር በሚደረግበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች ሊያጋጥሙን ይቸችላሉ፡፡ተማሪዎች የንግግር ትምህርትን በሚገባ እንዲገነዘቡና እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ ችግሮቹን በሚገባ በማወቅ ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

በድሉ (2007፡) እንደገለፁት ንግግርን በምንስተምርበት ጊዜ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች በማለት ጠቅሷቸዋል፡፡ እነዚህም መታቀብ፣ የሚናገሩትን ማጣት፣ ዝቅተኛ ሁሉን የማከለ ተሳትፎ ናቸው በማለት ገልጸዋል፡፡

1.**መታቀብ**:-ንግግር የሚያቀርብ ሰው ከሚያዳምጠው፣ ከሚያነበውና ከሚጽፈው ሰው የበለጠ የሌሎችን ሰዎች ትኩረት የመሳብ አቅም አለው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ የተለያዩ ንግግሮችን በሚያደርጉበት ወቅት ስለሚፈሩ ከመናገር እራሳቸውን ይቆጥባሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ትችትን በመፍራትና ንግግራችን የሌሎችን ሰዎች ስሜት አይስብም በማለት ሀሳባቸውን በዉስጣቸው ደብቀው በመያዝ በክፍል ዉስጥ ለመናገር ፍቃደኛ አይሆኑም፡፡

**2.የሚናገሩት** ማጣት:-ንግግር በተመረጠው ጉዳይ ላይ በቂ መረጃ ስለማይኖራቸው መናገር ቢፈልጉ እንኳን ለመናገር አይፈሩም፡፡ ተማሪዎች ለንግግር በተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ በቂ ዳራዊ እውቀት ካሌላቸው የንግግር ግላዊ ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል፡፡ ይህ አይነቱ ሁኔታ ከተከሰተ ተማሪዎች የንግግር ጥላቻን እያዳበሩ ይመጣሉ፡፡

**3.ዝቅተኛ ሁሉን ያላማከለ ተሳትፎ**:-አብዛኛውን ጊዜ የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራትን በአንድ ጊዜ የሚያሳትፉት አንድ ተማሪ ብቻ ነው፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ በርካታ ተማሪዎችን በንግግር ተግባር ላይ ማሳተፍ የቋንቋ ትምህርት ከተመደበው ጊዜ ጋር ሊጣጣም የማይችል ተግባር ነው፡፡ ይህ ሁኔታም የተወሰኑ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባርን በመቆጣጠር የሌሎች ተሳትፎ ውስን እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የንግግር ትምህርት በምናስተምርበት ጊዜ በትምህርቱ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱ የሚያደርሱ የተለያዩ ንግግርን የሚያደናቅፉ ተለዉጦዎች አሉ፡፡ እነዚህም ተለዉጦዎች ከፍተኛ ጭንቀት፣ በራስ መተማመን ማጣት፣ ፍረሀት፣ ዐይነ አፋርነት፣ ማህበረሰባዊ ባህል፣ ተነሳሽነት ማጣት፣ በቋንቋው ኢ አፈፊት መሆን፣ ለቋንቋው ያለ አመለካከት ናቸው፡፡

**ሀ.ከፍተኛ ጭንቀት**:-ሰው እራሱን ሳያስጨንቅ ሀሳቡን በነጻነት መግለጽ ለንግግር ትምህርት አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪዎች ንግግርን ለማድረግ በሚያስቡበት ሰአት የማወራው ነገር ለሌሎች አድማጮች ላይዋጥላቸው ይችላል፤

አይስባቸውም፤ ትክክል ላይሆን ይችላል፤ ሊጠፋብኝ ይችላል በማለት እራሳቸውን ያጨናንቃሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ተማርዎች በክፍል ዉስጥ የንግግር ትምህርት በሚማሩበት ሰአት የጭንቀት ባህሪ በዉስጣቸው እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

**ለ.በራስ መተማመን ማጣት፡-**አንድ ሰው ንግግር በሚቀርብበት ጊዜ በራስ መተማመን ቢኖረው ለንግሩ ሳቢነትና ማራኪነት እንዲሁም በንግግሩ መልእክት ለማስተላለፍ ጠቃሚና አስፈላጊ ነው፡፡ተማሪዎች የንግግር ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ የንግግር ተግባርን ሲያከናዉኑ የያዙት ሀሳብ ተክክል ላይሆን ይችላል ተቀባይነት ላያገኝ ይችላል በማለት በራሳቸው መተማመንን እንዳይኖራቸው ያደርጋቸዋል፡፡

**ሐ.ፍርሃት፡-**አነድ ተማሪ ያለዉን የንግግር ችሎታ አውጥቶ ለማሳየት እና በልበሙሉነት አውጥቶ ለማሳየት በራስ መተማመን ሊኖረው ይገባል፡፡ስለዚህ ተማሪዎች የንግግርን ተግባር በሚተገብሩበት ጊዜ አድማጭ ተመልካቾችን አይተው እንዴት በነዚህ ሰዎች ፊትለፊት እናገራለው፤ሰዎቹስ ምን ይሉኛል በማለት በዉስጣቸው የአይናፋርነት ስሜት ይታይባቸዋል፡፡እንደዚህ አይነት ሁኔታ ደግሞ ተማሪዎች የንግግር ትምህርትን በሚማሩበት ወቅት የሀፍረት ስሜት እንዲሰማቸው በማድረግ ፍረሀት እንዲነግስባቸው ያደርጋል፡፡

**መ.ዐይነ አፋርነት፡-**ሰዎች አንድን ንግግር በሚያደርጉበት ጊዜ በሰው ፊት ቆሞ በልበሙሉነት ሰውን ሳይፈራና ሳያፍር መናገር አለበት፡፡ተማሪዎች የንግግር ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ የንግግር ተግባርን ሲያከናውኑ በአይናቸው ሰውን ለማየት፣ ሰው ፊት ቆሞ ለመናገር ይፈራሉ፡፡ይህ ሁኔታ ደግሞ ተማሪዎች በንግግር ትምህርት ወቅት በራሳቸው በመተማመን የንግግር ትምህርት እንዳያከናውኑና የአይናፋርነት ባህሪ እነድኖራቸው ያደርጋል፡፡

**ሠ.ማህበረሰባዊ ባህል**፡-ሰው ያለምንም ጫና የተሰማውን ወይም በውስጡ ያለውን ሀሳብ በንግግር በገልጽ አጠቃሚ ነው፡፡ይህም ማለት ተማሪዎች የንግግር ትምህርትን በሚያከናዉኑበት ወቅት በማህበረሰብ ውስጥ በሚኖሩት ጫናዎች መሰረት ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለጽ ይቸገራሉ፡፡ይህ ሁኔታ ደግሞ ተማሪዎች በራስ መተማመናቸው እንዳይኀለብት በማድረግ ጫና ይፈጥርባቸዋል፡፡

**ረ.ተነሳሽነት ማጣት ፡-**አነድ ሰው ሀሳቡን በንግግር ለማቅረብ ተነሳሽነት ሊኖረው ይገባል፡፡ይህም ሲባል ተማሪዎች የንግግር ትምህርት በሚማሩበት ወቅት የንግግር ተግባርን ለማከናወን ተነሳሽነት አይኖራቸዉም፡፡ይህም የሚሆንበት ምክንያት ተማሪዎች ግዴለሽነትና ምናለብኝነት ስለሚታይባቸው ይህ ሁኔታ ደግሞ ተነሳሽነት እነድይጡ ያደርጋል፡፡

**ሰ.በቋንቋው አአፈፌት መሆን፡-** አነድ ሰው ሀሳቡን በንግግር በሚገባ ለመግለጽ ቋንቋውን በተሸለ ሁኔታ ማወቅ ይኖርበታል፡፡ይህም ማለት ተማሪዎች የንግግር ትምህርትን በሚማሩበት ጊዜ የንግግር ተግባርን ለማከናወን በሚፈልጉበት ሰአት የቋንቋ ችግር ይፈጠራል፡፡ይህ ደግሞ ተማሪዎች የንግግር ተግባሩን በሚገባ እንዳያከናዉኑና የንግግር ችሎታቸውንም እነዳያዳብሩ እነቅፋት ይሆንባቸዋል፡፡

**ሸ.ለቋንቋው ያለ አመለካከት ፡-**ሰው በንግግር ሀሳቡን ለመግለጽ ከፈለገ ለቋንቋው ጥሩ አመለካከት ሊኖረው ይገባል፡፡ስለሆነም ተማሪዎች በክፍል ዉስጥ የንግግር ትምህርትን በሚያከናዉኑበት ጊዜ ሁለተኛ ቋንቋን እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ እንችለዋለን ወይም ይጠቅመናል ብለው ስለማያስቡ ለቋንቋው የሚኖራቸው አመለካከት ዝቅተኛ ነው፡፡ስለዚህ ተማሪዎች ለቋንቋው የሚኖራቸው አመለካከት ዝቅተኛ ከሆነ የንግግር ችሎታቸው ላይ ከፍተኛ ጫና ያደርጋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የጥናቱ ንድፍና ዘዴ

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በዋናነት የሚያተኩረው አይነታዊ የምርምር ዘዴ ሲሆን በክለሳ ድርሳናት ላይ የሚነሱ ነጥቦችን መሰረት በማድረግ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን እንደተገቢነታቸው በቃላት አማካኝነት በገለጻ ስልት ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም በአሀዛዊ መረጃዎች መጠናዊ የምርምር መተነተኛ ስልት የተጠቀመ ነው፡፡

### 3.2. የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት የተለያዩ ለመረጃ ምንጭነት ያገለግሉኛል ብሎ አጥኚው ያሰባቸዉንተጠኚዎችንተመርጧል፡፡ በዚህም ሁኔታ የትምህርት ቤት፣ የመምህራን ፣ የተማሪዎች ናሙና መረጣ ተካሄዷል፡፡ እነዚህ የናሙና መረጣዎች ለአጥኚው ጥሩ መረጃ የሚያስገኙ ነቸው፡፡ እነሱም እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ውስጥ ቀርበዋል።

#### 3.2.1. የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ኩዩ ወረዳ ከሚገኙ ሁለት ትምህርትቤቶች ዉስጥ ብሪቲ ሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ይህ ትምህርት ቤትም የተመረጠበት ምክንያት አንዱ ትምህርትቤት በጸጥታ ምክንያት ስለ ተዘጋ ብሪቲ ሁለተኛ ደረጃ በጠቅላይ ናሙና ተመርጧል፡፡በሌላ በኩልምየተመረጠዉ ትምህርት ቤትለአጥኚው ቅርበት ያለዉ ሲሆን አጥኚው መረጃዎችን ለመሰብሰብምቹሁኔታ ስለሚፈጠር ሊመረጥ ችሎዋል፡፡

#### 3.2.2. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ኩዩ ወረዳ ብሪቲ ሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት ዉስጥ የሚያስተምሩ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ሁለትናቸዉ፡፡እነዚህም መምህራን በጠቅላይ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠው የጥናቱ ተተኳሪሆነዋል፡፡ እነዚህ መምህራን በጠቅላይ ናሙና የተመረጡበት ምክንያት በትምህርት ቤቱ ዉስጥ ያሉት የአማርኛ ቋንቋ

መምህራን ሁለት በመሆናቸው ነው፡፡ የመምህራኑን ዳራዊ ሁኔታቸዉን ስንመለከት ሁለቱም መምህራን ወንድ ሲሆኑ የትምህርት ደረጃቸው አንደኛ ዲግሪ ሲሆን ስምንትና አምስት አመት የስራ ልምድ አላቸዉ፡፡

#### 3.2.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ከላይ ከተጠቀሰዉአንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በተመረጡት ሶስትምዴቦች ውስጥ በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ በአማካይ 40-42 ተማሪዎች ይገኛሉ፡፡የመነሻ ቁጥር በዕጣ ከተለየበኋላአንድአልፎ አንድበመውሰድከእያንዳንዱክፍልሃያ(20) በአጠቃላይ ስልሳ(60) ተማሪዎች በተራ የዕጣ ናሙና ዘዴ ተመርጠው የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞላተደርጓል፡፡ ተማሪዎቹ የጽሁፍ መጠይቁን እንዲሞሉየተደረገውየክፍል ውስጥ ምልከታውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ምክንያቱም ምልከታና የጽሁፍ መጠይቁ ተመጋጋቢዎች ናቸው ተብሎ ስለታሰበ ነው፡፡ከተማሪዎቹ የሚሰበሰበው መረጃም በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ያጠናክራል ፡፡

### 3.3. የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የአስረኛክፍል መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበርን የሚመለከት ነው፡፡የጥናቱ አካባቢ፣የትምህርት ቤቱ፣የመምህራን እና የተማሪዎቹ ናሙና ከተመረጡ በኋላ መረጃ የመሰብሰቡ ስራ ተከናውኗል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎች አስተማማኝ ይሆኑ ዘንድም በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተጠቅመዋል፡፡ በመሆኑም ለጥናቱ መረጃዎች ለማሰባሰብ ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

#### 3.3.1. የክፍል ውስጥ ምልከታ

በተጠኚ ትምህርት ቤት ውስጥ የተስተዋለው የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የመማር ማስተማር ክንውን ለመታዘብ በቼክሊስት የተደገፈ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያነትበጥቅም ላይ ውሎል፡፡ምልከታ የተመረጠበት ምክንያት ጥናቱን ተጨባጭ ለማድረግ

ነው፡፡ምልከታው በትምህርትቤቱ ውስጥ የሚያስተምሩትን የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አካቷል፡፡ምልከታው ውስንየምልከታ ስሌትን መሰረት ያደረገ ሲሆን በዚህ ውስን የምልከታ ስሌት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደትላይ ከሚተገበሩ ክንውኖች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች በተዘጋጀው የመከታተያ ቅጽላይ በመሙላት መከናወን ወይም አለመከናወኑን በማየት እንዲረጋገጥ ተደርጓል፡፡

### 3.3.2. የጽሁፍ መጠይቅ

የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበርን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብእንዲቻልለ60 (ስልሳ)ተማሪዎች የፅሐፍ መጠይቅ ቀርቧል፡፡አጥኚው የጽሁፍ

መጠይቅ የመረጠበት ምክንያት ተጠኚዎቹ በምልከታ ከታየው በተጨማሪ ሀሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ ነው፡፡የፅሐፍ መጠይቁ መሰረታዊ አላማ በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች የተገኘውን ውጤት ለማገናዘብ እና ትክክለኛነቱንየማረጋገጥ ነው፡፡ ይህም የፅሐፍ መጠይቅ በአማካሪይ ተገምግሞና አስፈላጊው ማሻሻያ ተደርጎበት በስራ ላይ ውሎል፡፡የፅሐፍ መጠይቁ በተቻለ መጠን ግልጽ ቋንቋን በመጠቀም የተዘጋጀ ሲሆን አጥኚዉበትምህርት ቤቱ በመገኘት በናሙናነት የተመረጡትን ተማሪዎች ለብቻቸው በመለየት ስለመጠይቁ አጠቃሊይ ዓላማ እና አሞላል ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላበየግላቸው እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡

### 3.3.3. የቃል መጠይቅ

ከጽሁፍ መጠይቅና ምልከታ በተጨማሪ ቃለ መጠይቅም የዚህ ጥናት አጋዥ የመረጃ መሰብሰብያ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡አጥኚው ቃለመጠይቅ የመረጠበት ምክንያት ተጠኚዎች ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ከአንደበታቸው ለማግኘት ስለሚያስችል ነው፡፡ቃለ መጠይቁ በጥናቱ ተተኳሪ በሆነው ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚገኙየአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ሲሆን አላማውም መምህራኑ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንግግር ክሂልን እንዴት እንደሚያቀርቡ፣ ስለ ቋንቋው ንግግራዊ አቀራረብ ያላቸውን ግንዛቤ የመረዳትና በአተገባበሩ ላይ ስለሚያጋጥሙ ቸግሮች መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪም ቃለ መጠይቁ የመምህራንን ዳራዊ መግለጫየሚይዝ ሲሆን ለጥናቱእንዲስማማ ሆኖ ከተዘጋጀ በኋላ በአማካሪዬ ተገምግሞና አስፈላጊ ማሻሻያ ተደርጎበት ስራ ላይ ውሎል፡፡

## 3.4. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

በዚህ ጥናት ከመምህራን ቃለ መጠይቅ፣ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅና ከምልከታ ከተሰበሰቡት መረጃዎችና ውጤቶች በመነሳት በምዕራፍ አንድ ስር የቀረቡት የዓላማ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት ትንተና የሚደረግበት ስልት ዓይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴዎች ሥራ ላይ ይዉላሉ፡፡ ትንተናው መረጃዎቹ በሚያነሱት ጉዳይ መሰረት ይቀርባል፡፡ሌላው በመረጃ ትንተና የታየው ውጤት የሚብራራበት ነው፡፡ውጤቱንም ከቀረቡት ይዘቶች እና ክንውኖች፤ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከሚሰራበት ዘዴ እና አተገባበር፤ በክለሳ ድርሳናት ቅኝት ስር ከሰፈሩትንድፍሃሳቦች ጋር መጣጣማቸውን የመፈተሽ መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ እንዱሁም ከዘዴው ውጤታማነት አንፃር ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ እንዴት እደሚተገበርና የአቀራረብ ውጤታማነትን መገምገም ነው፡፡ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል አተገባበርን በተለያዩ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን ቀረበዋል፡፡ ስለሆነም በምዕራፍ ሶስት የመረጃ መሰብሰብያ ናቸው ተብለው የቀረቡት ምልከታ፣ የጽሁፍ መጠይቅ እና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡እነዚህን መረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎችን በመጠቀም የተሰበሰቡትን መረጃዎች ተተንትዋል፡፡

### 4.1. ከምልከታ፣ ከጽሁፍ መጠይቅ እና ከቃለ መጠይቅ መረጃወችንመተንተን

#### 4.1.1. ከምልከታ የተገኘ የመምህራን የንግግር ክሂል ትምህርት አተገባበር ትንተና

*4.1.1.1. የመምህራን የንግግር ክሂልትምህርት የአቀራረብ ትግበራ ሁኔታ ትንተና*

የንግግር ትምህርት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በምንደርግበት ወቅት የተምህረቱ አቀራረብ ዋና እና አስፈላጊው ተገባር ነው፡፡ ስለሆነም የንግግር ተምርት ትልቁ አላማ ተማሪዎች ወደ ትምህርቱ ዋና ስራ ከመግባታቸው በፊት የትምህርቱን አላማ ግልጽ አድርጎ መናገር፣ ተማሪዎች የመናገር ችሎታቸውንና ፍላጎታቸውን በተለያየ መንገድ መግለጽ እንዲችሉ ማድረግ፣ የእለተ እለት ገጠመኞቻቸውን ከራሳቸው ታሪክና ከትምህርታቸው ጋር አያይዘው የሚገልጹበትን ሁኔታ ማዘጋጀት፣ በክፍል ውስጥ የተማሩትንና የተገነዘቡትን መግለጽ እንዲችሉ የማነቃቃት ስራን መስራት የንግግር ክሂል ትምርትን በሚፈለገው ሁኔታ ተገባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የንግግር ክሂል ተግባራዊ ለማድረግና የንግግር ተግባሩን በምን አይነት መንገድ ማቅረብ እንዳለባቸው የተለያዩ ምሳሌዎችንና ሀሳባቸውን ሳይፈሩ በግልጽ መናገር እንዲችሉ ማድረግ የመምህሩ ከፍተኛ ሚና ነው፡፡ ስለዚህ የንግግር ተምህረቱን በይበልጥ ሊያስረዱ የሚችሉ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የእለት ትምህርታቸውን አላማው ምን እንደሆነ በመናገር ምን አይነት ተግባራትን በቅደም ተከተል ማቅረብ እነዳለባቸው እነዲያውቁ ማድረግ፣ ስለ እለቱ ተግባር ግልጽ መመሪያ መስጠትና መመሪያዎቹን ደግሞ በሚገባ መረዳታቸውን ተገቢ በሆነ መንገድ ማረጋገጥ የመምህሩ ዋና ተግባር ነው፡፡ እነዚህን ተግባራት ደግሞ ለማከናወን ና ተግባራዊ ለማድረግ በዋናነት ያለው የተማሪዎች አቀማመጥ ና የክፍሉ ሁኔታ ትልቅ ሚና ስላለው መምህሩ እነዚህን ጉዳዮች ማስተካከል አለበት፡፡

ከላይ ኪተነሳው ሀሳብ በመነሳት ከተዘጋጀው የምልከታ ቅጽ መሰረት በማድረግ የከፍል ውስጥ የንግግር ክሂል አተገባበርን በተመለከተ የተገኘውን መረጃ በተለያዩ ክፍሎች በመክፈል ቀርቧል፡፡ በክፍል ምልከታ ወቅት በተተኳሪነት የቀረቡ ነጥቦች መከናወን አለመከናወናቸውን መከታተል የተቻለ ሲሆን ለእያንዳንዱ የንግግር ክሂል አቀራረብ ከነውኑን ከምልከታ ቅጽ የተገኘውን መረጃ እንደሚከተለው ትንተና ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ 1. የመምህሩ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ተምህርት ተግባራትን አቀራረብን**

**በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ ውጤት የሚያመለክት መግለጫ**

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የትምህረቱአላማለተማሪዎችበግልጽቀርቧል? | 3 | 75% | 1 | 25% |
| 2 | ትምህርቱሲቀርብየመማሪያመጽሀፍትንመሰረትንየደረገነው? | 4 | 100% | ----- | ---% |
| 3 | የትምህርቱአቀራረብየማስተማሪያመሳሪያዎችንመሰረትያደረገነው? | - - - - | --- % | 4 | 100% |
| 4 | የትምህርቱአቀራረብሂደትተማሪዎችንያሳተፈነው? | 1 | 25% | 3 | 75% |
| 5 | የትምህርቱአቀራረብየተማሪዎችንየእውቀትደረጃቸውንያማከለነው? | 4 | 100% | ---- | ---% |
| 6 | ተማሪዎችየንግግርትምህርትንእንዲለማመዱይበረታታሉ? | 2 | 50% | 2 | 50% |
| 7 | የቀረቡትየትምህርትመመሪያዎችለተማሪዎችግልጽናቸው? | 3 | 75% | 1 | 25% |

በዚህ ሰንጠረዥ ውሰጥ እንደ ተገለጸው የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርትን በሚተገበሩበት ወቅት በተደረገው የምልከታ ክትትል የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ትምህርትን ለማዳበር የንግግር ተግባራትን ክፍል ውስጥ ከማከናወናቸው በፊትና የእለቱን ትምህረት ከማቅረባቸው በፊት አለማን በግልጽ ያቀረበው 3 (75%) ሲሆን፤ የተምህረቱን አላማ ሳይገልጹ ወደ እለቱ የትምህረት ትግበራ የገቡው ደግሞ 1 (25%) ነው፡፡

አንድ መምህር አንድን ትምህርት በሚያስተምርበት ወቅት ስለ ትምህርቱ ምንነት እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡ ስለዚህ አንድ መምህር ክፍል ገብቶ የዕለቱን ትምህርት ከመቅረቡና ከማስተማሩ በፊት አላማውን በሚገባ ለተማሪዎች ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡ በማስከተልም ተማሪዎቹ የመጡበትን ማህበራዊ የአኗኗር ስረአት፣ የተምህርት ደረጃ፣ የእድሜ ደረጃቸውንና የውስጥ ፍልጎታቸውን፣ ያሉበትን የትምህረት ደረጃና የመጡበትን ማህበረሰብ ባህልና ወግ መረዳት አስፈላጊ ነው፡፡ በማያያዝም የተማሪዎችን የንግግር ችሎታቸውን የሚያዳብሩ፣ ተነሳሽነታቸውን የሚያነሳሱ ተሳትፎአቸውን የሚያጠናክሩ በተጨማሪም ተመሪዎቹን የሚያወያይና የሚያከራክሩ የትምህረት ርዕሶችን መርጦ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች እንዲ ተገብሩ ማድረግ ጠቀሜታው የላቀ ነው፡፡

ከላይ በምልከታው ለማየት እንደ ቻልነው ውስን መምህራን የዕለት ትምህርት አላማውን መግለጽ ሲችሉ፤ ሌሎች ግን የትምህረቱን አላማ ሳይገልጹ በቀጥታ የእለቱን ትምህረት ወደ ማስተማር ገብተማል፡፡ ስለሆነም የንግግር ትምህርት በክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት ግልጽ አላማ በመስጠት በኩል የተሻለ ቢሆንም ግን የተወሰኑ ጉድለቶች እንዳለበት ያመለክታል፡፡ በመቀጠልም የዕለቱ ትምህረት አቀራረብ የተማሪ መማሪያ መጽሀፍትን የማድረጉ ሂደት4 (100%) መሆኑ የትምህረቱን መረሀ ትምህርትና ስረአተ ትምህረቱን መሰረት ያደረገ እንደ ሆነ ያመለክተናል፡፡

ከዚህ ሀሳብ ጋር የሚያያዘው ልላው ጉዳይ የንግግር ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲተገበሩ ተተኳሪ መምህራን የዕለቱን ትምህረት በሚያቀርቡበት ጊዜ የማስማሪያ መረጃ መሳሪያዎችን መሰረት የደረገ አልነበረም፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚከናወን የንግግር ማስተማር ሁኔታ ደግሞ የተማሪዎቹን ፍላጎትና የመጡበትን ከባቢያዊ ሑኔታ የላገናዘበ ስለሚሆን የተሟላ አያደርገውም፡፡

የንግግር ትምህርት በክፍል በውስጥ በሚተገበርበት ወቅት የተለያዩ ተግባራትን እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸውና የሚተላለፈው ነገር የማያሻማ መሆኑን በማወቅ የተማሪዎችን የትመሀርት ደረጃቸውንና ፍላጎታቸውን በሚያሟላ መንገድ የተለያዩ ትምህረት ማሳያዎችን በማቅረብ ወደሚፈለገው የትምህርት ወይም የንግግር እውቀት ደረጃ ማስገባት የመምህራን አስፈላጊው ተግባር ነው፡፡ በመቀጠልም መምህራን የንግግር ትምህርትን ተግባርን በሚያከናዉኑበት ሰአት የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት በመመልከት በክፍል ውስጥ እንዲሳተፉ የማበረታታትና ተነሳሽነት እነዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ የዕለቱን ትምህርት ሂደቱ ተማሪን የሳተፈ የቀረቡት 1 (25%) ሲሆን ተማርን ያልሳተፈ የትምህርት ሂደትን አቀራረብን የተከተሉት ደግሞ 3 (75%) ናቸው፡፡

እንደሚታወቀው አንድ መምህር የንግግር ትምህረት በሚተገብረውበት ወቅት የተማሪዎችን ተሳትፎ በሚገባ መተግበር አለበት፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በመምህር መሪነት የንግግር ትምህረት ተግባራትን በራሳቸው መንድ ማከናወን ካልቻሉ ተጋባራዊነቱና ውጤታማነቱ ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች በገባቸውና በተረዱት መንገድ ተሳትፎዋቸውን ማሳደግ የመምህሩ ተግባር ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት ከተከታታይ ምልከታው እንደ ተገለጸው የተማሪን ተሳትፎ የተገበሩት በጣም አነስተኛ ሲሆን ተማሪውን ያላሳተፉትና ለራሳቸው ተግባሩን በመናግር ብቻ ያለፉት ደግሞ ከፍተኛ በመሆኑ ተማሪን በማሳተፍ በኩል ያለው ሁኔታ በጣም ደካማ ነው፡፡

የንግግር ትምህርትን በክፍል ውስጥ ከመተግበሩ በፊት መምህር ቅድሚያ የተማሪዎቹን የእዉቀት ደረጃ በሚገባ ማወቅ አለበት፡፡ ይህም ሲባል አንድ መምህር የንግግር ትምህቱን ለመማር የተዘጋጁት ተማሪዎች እነማናቸው፤ ለነዚህ ተማሪዎችስ በምን አይነት መንገድ ትምህረቱን ባቀርብ ይገባቸዋል፤ ተምህርቱን የአወሳሰድ ሁኔታቸውስ ምን ይመስላል የሚሉ ሀሳቦችን በደንብ ሊያውቅ ይገባል፡፡ ከዚህም በመነሳት ለተማሪዎች በእውቀታቸው ልክ የሚመጥናቸውን ትምህርት የመስጠት ተግባር አስፈላጊው የመምህራን ተግባር ነው፡፡

ከምልከታው ትኩረት እንደ ተገለጸው የዕለት ትምህረት የተማሪዎችን የዕውቀት ደረጃ ያማከለ አቀራረብ ተግባራዊ ያደረጉት 4 (100%) ናቸው፡፡ ከዚህ እንደምንረዳው የንግግር ትምህርትን በሚያቀርቡበት ወቅት የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ የማከለ ትምህረት በሚገባ አቅረበዋል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መምህራን የንግግር ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎች የተማሩትን፣ የተመለከቱትን፣ የተረዱትን ና የተገነዘቡትን ነገር በተግባር እንዲያሳዩ ና በተግባር እንዲያከናውኑ ማድረግ ከፍተኛ ድርሻቸው ነው። ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑና የተለያዩ ንግግሮችን በማድረግ ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ የመምህራን ትልቁ ሀላፊነት ነው። ይህንንም መነሻ በማድረግ ከምልከታ በተገኘው መረጃ በክፍል ውስጥ የእለት ትምህርት በሚተገበሩበት ወቅት የንግግር ትምህርትን እንዲለማመዱ የማድረጉሂደት ላይ እንዲለማመዱ ያደረጉት 2 (50%) ሲሆን ያላለማመዱት ግን 2 (50%)ነው። በዚህም ሁኔታ መምህራን የንግግር ትምህርት ላይ ተማሪዎችን የማለማመዱ ነገር ከመረጃው እንደተገለፀው በተወሰነ ደረጃ ያከናወኑት ቢኖርም ግን በእኩል ደረጃ ተግባሩ አልተከናወነም። ከዚህ የምንረዳው የንግግር ትምህርት የማለማመዱ ነገር በጣም ደካማ እንደሆነ ነው።

መምህራን የንግግር ክሂልን በሚያስተምሩበት ወቅት የትምህርቱን መመሪያ ግልፅ ማድረግ አስፈላጊው ተግባር ነው። ተማሪዎች የሚማሩትን ነገር እንዲረዱትና በሚገባ እንዲገነዘቡት እንዲሁም ከሚማሩት ትምህርት አስፈላጊውን እውቀት እንዲያገኙ መመሪያውን በሚገባ ግልፅ አድርጎ መናገር የመምህር ሚና ነው። መመርያን በግልፅ በክፍል የእለት ትምህርት ጊዜ መምህራን ለተማሪዎች አለመናገርና አለ መግለፅ የሚፈለገውን የንግግር ክሂል ትምህርት ከግብ ለማድረስ በጣም አስቸጋሪ ነው። ስለዚ አንድ መምህር የእለት ትምህርትን ከማቅረቡ በፊት የትምህርቱን ትምህርት በግልፅ መናገር ይኖርበታል። ከዚህ በመነሳት ከምልከታ ቅፅ ላይ እንደ ተገለፀው የእለት ትምህርት ከመቅረቡ በፊትየትምህርቱ መመሪያ ያቀረቡት 3 (75%) ሲሆኑ ያላቀረቡት ግን 1 (25%) ነው። ይህም ማለት መመሪያን ግልፅ ያደረጉት በአብዛኛው ቢሆንም ግን በተወሰነ ሁኔታ ጉድለት እንዳለው ያመለክታል። ይህ ደግሞ የትምህርት ሂደቱን ከግብ ለድረስ አስቸጋሪ ሊያደርገው ይችላል።

ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ በምልከታው ለመግለፅ እንደተሞከረው መምህራኑ የእለት ትምህርታቸውን ከማቅረባቸው በፊት መማሪያ መፅሀፍት መሰረት ያደረገ ትምህርት ና የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ያማከለ ትምህርት ማቅረብ ላይ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደረጉ ሲሆን የማስተማሪያ መሳሪያዎችን መሰረት ያደረገ የትምህርት አቀራረብ ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ና ተግባራዊ አይደለም። ሌሎቹ ደግሞ በግማሽ የተከናወኑና ያልተከናወኑም አሉ ። ስለዚህተግባራቱ በተወነ ደረጃ የተከናወኑ እንዳሉ ሁሉ ያልተተገበሩም አሉ።

*4.1.1.2. የተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ የመለማመድ ተግባራትን*
**የተመለከተ ትንተና**

የንግግር ትምህርት በፍል ውስጥ በሚከወንበት ወቅት ዋናና አስፈላጊው ነገር ተግባር ነው። የንግግር ክሂል ትምህርት በተግባር እየ ተከወነ የማይተገበር ከሆነ ውጤታማነቱ በጣም ዝቅተኛ ነው። ስለዚ አንድ መምህር የንግግር ትምህርትን በእለት ትምህርታቸው ውስጥ በሚተገበሩበት ወቅት የተለያዩ የንግግር ተግባራትን ተማሪዎች እንዲያከናው ማድረግ ከፍተኛ ሚና አላቸው። ስለዚህ ከምልከታ የተገኙትን መረጃዎችን እንደሚከተለው ለመከታተል ተችለዋል።

**ሰንጠረዥ 2. የተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግርክሂል ትምህርትን የመለማመድ ተግባራት**

**የተመከተ ከምልከታ የተገኘ መግለጫ**

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 8 | በልምምድ ጊዜ ተማሪዎች በደንብ ይሳተፋሉ? | 1 | 25% | 3 | 75% |
| 9 | ንግግርን ለመለማመድ የተሰጣቸውን ጊዜ በአግባቡ ተጠቅመዋል? | 2 | 50% | 2 | 50% |
| 10 | የንግግር ክሂል ማጎልበቻ ተግባራትን (ክርክር፣ውይይት፣ጭውውትና ሌሎች) ተግባራትን አከናውነዋል? | 2 | 50% | 2 | 50% |
| 11 | የንግግር ልምምድን በግልና በቡድን አከናውነዋል? | 3 | 75% | 1 | 25% |

ከላይ በተሰጠው ሰንጠረዥ ውስጥ እንደ ተገለፀው የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት የንግግር ትምህርቱን እውቀት በሚገባ ለማዳበር እና እውቀቱን በሚገባ ለማካበት ትልቁ ተግባር ልምምድ ነው። የንግግር ትምህርት በተግባር መደገፍ አለበት። በተግባር ያልተደገፈ የንግግር ክሂል ትምህርት ከግብ ለማድረስ አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች የሚማሩትን ነገር በክፍል ውስጥ በተግባር ማሳየት እና ከትምህርት ቤት ውጪም በሚገባ በነፃነት በራሳቸው በገባቸው ቋንቋ የራሳቸውን ሀሳብ መግለፅ ይኖርባቸዋል።

Bymen (1986:34) እንደገለፀው፣ በልምምድ ጊዜ በሚቀርበው የትምህርት ዐውድን መሰረት በማድረግ በቋንቋው በመጠቀም የንግግር ችሎታቸውን ለማዳበርና በሚገባ ለማሳደግ የተለያዩ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት ወቅት ነው። ስለዚህ መምህሩም አስፈላጊውን እገዛና ሁኔታዎችን ለተማሪዎች ሊያመቻችላቸው ያስፈልጋል። ይህ ማለት ተማሪዎች የንግግር ትምህርትን በክፍል ውስጥ በሚተገበሩበት ወቅት ልምምድ ማድረግ አለባቸው። ልምምዱንም በሚያደርጉበት ጊዜ ተማሪዎች በገባቸውና በተረዱት መንገድ በራሳቸው ቋንቋ ሀሳባቸውን መግለፅ እንዲችሉ ማድረግ የመምህራን ከፍተኛ ሚና ነው።

ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት በሚተገበሩበት ወቅት ተማሪዎች በሚገባ ትምህርቱን በተግባር እና በነፃነት መግለፅ እንዲችሉ ማገዝና ማበረታታት እንዲሁም ማመቻቸት አስፈላጊ ነው። ከዕለቱ ትምህርት የክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘ መረጃን ስንመለት በንግግር ክሂል ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች በደንብ የመሳተፍ ሁኔታ ተግባራዊ ያደረጉት 1(25%) ሲሆን ተማሪዎቹ ያልተሳተፉበት ደግሞ 3 (75%) ናቸው። ይህም ማለት የንግግር ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች የመሳተፉ ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ ነው። ምክንያቱም ከተደረጉት ምልከታዎች ውስጥ በብዛት የተማሪዎች ተሳትፎ በብዛት አልታየበትም።

የንግግር ትምህርትን አንድ መምህር በሚያስተምርበት ጊዜ ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት እንዲለማመዱ ማድረግ ብቻ ሳይሆን ለተግባሩ የተሰጣቸውንም የገዜ ገደብ ጠንቅቀው መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊው ተግባር ነው። ይህም ሲባል አንድ ተማሪ የንግግር ትምህርትን በሚማርበትና በሚለማመድበት ወቅት በስንት ጊዜ ውስጥ ምን ተናግሮ መጨረስ እንዳለበት የማስገንዘብና የማለማመድ ከፍተኛ ሚና የመምህራን ነው። ተማሪዎች በምን ሰአት ምን እንደሚናገር፣ እንዴት ጀምሮ መጨረስ እንዳለበት፣ ሰአቱ በአግባቡ ካልጠቀመ ምን ተፅኖ እንዳለው ሁሉ የማስመዝገንዘብ ሀላፊነት የመምህራን ነው። በምልከታው የክፍል የንግግር ትምህርት እንደቀረበው መረጃ የንግግር ክሂል ትምህርት በሚከወንበት ወቅት ልምምድ ሲያደርጉ የተሰጣቸውን የጊዜ ገደብ በአግባቡ እንዲጠቀሙ ያደረጉት 2 (50%) ሲሆኑ ያላደረጉት ደግሞ 2 (50%) ናቸው። ከዚ እንደምንረዳው የንግግር ክሂል ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች ልምምድ ሲያደርጉ የተሰጣቸውን ጊዜ በአግባቡ እንዲጠቀሙ በማድረግሂደት ግማሹ እንዲጠቀሙ የማድረግ ሁኔታ ሲኖር ያላደረጉት ደግሞ ግማሽ ናቸው። እሄ ደግሞ ጉድለት እንዳለው ያሳያል።

የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት መምህራን የተለያዩ ተግባራትን እንዲተገብሩ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ የንግግር ትምህርት በሚከወንበት ጊዜ የሚተገበሩ ተግባራት ተማሪዎች የተለያዩ ርዕሶችን በመምረጥ መከራከር እንዲችሉ ማድረግ፤ እርስበርስ በሚማሩት በክፍል ውስጥ በተሰጣቸው ነገር እንዲወያዩ ማድረግ፤ የተለያዩ የህይወት ገጠመኞቻቸውን በማምጣት ጭውውት እንዲያቀርቡ ማድረግ የመምህሩ ከፍተኛ ተግባር ነው፡፡ ይህም ሲባል ተማሪዎች

በክፍል ውስጥ የተማሩትን የንግግር ትምህርት ተግባራትን እርስ በርስ ከተከራከሩና ከተወያዩበት እንዲሁም ገጠመኞቻቸውን በጭውውት መልክ ካቀረቡ የንግግር ተግባራቱን ለመከወንና ንግግር ለማድረግ ጥሩ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

ሆኖም በሰንጠረዡ ውስጥ በምልከታ በተገኘው መረጃእንደ ተገለጸው መምህራን የእለት ትምህረት በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህረት ሲተገበሩ የንግግር ክሂል ማጎልበቻ ተግባራትን፣ ክርክር፣ ውይይት፣ ጭውውትና ሌሎች ተግባራትንም ያከናወኑት 2 (50%) ሲሆኑ ተግባሩን ያላከናወኑት ደግሞ 2 (50%)ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ የሚያመለክተው ተግባር ላይ የዋሉ ክንውኖች ቢኖሩም ያለተተገበሩ የንግግር መተግበሪያ ሁኔታወች ስራ

ላይ እንዳልዋሉ ያሳየናል፡፡ ስለሆነም የንግግር ክሂል መተግበሪያ ተገባራት በክፍል ውሰጥ ስራ ላይ ካልዋሉ የንግግር ትምህርትን ከግብ ለማድረስ ያስቸግራል፡፡

የንግግር ትምህረትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት ተግባራቱን ስራ ላይ ማዋል ብቻ ሣይሆን እንዴት እንደሚተገብሯቸው እንዲረዱ ማድረግም አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎችም እነዚህን የንግግር መተግበሪያ ተግባራትን በተለያዩ ሁኔታዎች እነዲያከናውኑ ማድረግ የመምህሩ ሚና ነው፡፡ የንግግር መተግበሪያ ሁኔታዎች በቡድን፣ በግልና በጥንድ ተማሪዎች እንዲተገብሯቸው ማስገንዘብና እንዲያከናውኑ ማድረግ የመምህራን ተግባር ነው፡፡ ስለዚህ በምልከታ ቅጽ ላይ መምህራን የዕለቱን የንግግር ክሂል ትምህርትን ተግባራዊ ሲያደርጉ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለከተው የንግግር ልምምድን በግልና በቡድን ያከናወኑት 3 (75%) ሲሆኑ ተግባሩን ያላከናወኑት ደግሞ 1 (25%) ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው የንግግር ልምመድ ወቅት የግልና የቡድን ተገባርትን ተማሪዎች እንዲ ሰሩ ያደረጉት ከፍተኛ ቁጥር ሲኖራቸው ያላከናወኑ መምህራን ጥቂቶች እንዳሉ ያመለክታል፡፡ ይህ ደግሞ በተወሰነ ሁኔታም ቢሆን ትምህረቱ ላይ ጉድለት እንደሚፈጥር ያሳያል፡፡

ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ ለመግለጽ እንደተሞከረው መምህራን የዕለት ትምህርታቸውን በሚተገብሩበት ወቅት የንግግር ትምህርትን ሲያከናውኑ የምልከታው መረጃ እንደሚያመለከተው በንግግር ልምምድ ጊዜ ተግባራቱን ያከናወኑት ከፊሎቹ ሲሆኑ ያላከናወኑትም መምህራን እንዳሉ ለመገንዘብ ተችሎዋል፡፡

*4.1.1.3. የተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ*
**በተመለከተ ትንተና**

የንግግር ትምህረት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ በሚገባ የማከለ መሆን ይኖርበታል፡፡ መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት ተማሪዎች ተሳትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታት ና እርስ በርስ የመወያየት ባህል እንዲያዳብሩ ማድረግ ከፍተኛ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ይህም እንደሚያመለክተው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የንግግር ተሳትፎዋቸውን የሚያሳድጉና የሚበረታቱ ከሆነ የንግግር ችሎታቸውን በሚገባ ማሳደግ ይችላሉ ማለት ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 3. የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ትምህርትንበክፍል ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ**

**የተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መግለጫ**

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 12 | የንግግር ክሂልን የማስተማር ሂደቱ ሁሉንም ተማሪዎች ያሳተፈ ነው? | 1 | 25% | 3 | 75% |
| 13 | የመፍራትና የመናገር ልምድ የሌላቸው ተማሪዎች እንዲበረታቱ ተደርጓል? | 4 | 100% | - - - | - - - |
| 14 | በንግግር ልምምድ ወቅት ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን እንዲያከናውኑ ተደርጓል? | 1 | 25% | 3 | 75% |
| 15 | በሚለማመዱበት ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ የመወያየት ባህል እንዲኖራቸው ይደረግ ነበር? | 2 | 50% | 2 | 50% |

Harmer (2007) የንግግር ክሂል ለማሳደግ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ሊያሳትፉ የሚችሉ ተግባራት መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡ የንግግር ክሂል ተግባራት ሲዘጋጅ ተማሪዎቹ ሙሉ በሙሉ በትምህርቱ እነዲሳተፉ እድል የሚሰጡና ከልምምዱ በኋላ የመምህሩ ምጋቤ ምላሽ ግምት ውስጥ የሚያስገቡ ከሆነ ተማሪዎቹ በትምህርቱ እርካታ ያገኛሉ፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የታለመውን አላማ በቀላሉ እንዲደርሱበት ይረዳል፡፡ ተግባራቱ ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፍ ከሆነ ክፍሉ ያለ ምንም ችግር

ተግባቦቱ የሰመረ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹን በራስ የመተማመን ስሜት ከፍ በማድረግ በንግግር ሀሳብን መግለጽ የቋንቋ ትምህረት ክፍል ባህል እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል በማለት ይገልጻሉ፡፡ ስለዚህ የተማሪዎችን ተሳትፎ እንዲያድግና ተከታታይነት እንዲኖረው መምህራን መተማመናቸው እንዲጨምር ማድረግ የመምህሩ ሚና ነው፡፡ ይህም ማለት መምህሩ የንግግር ትምህርትን በሚያስተምርበት ወቅት የንግግር ተግባራትን የተለያዩ መልመጃዎችን በራስ ከመስራት ይልቅ ተማሪዎች በተግባር ሰርተው እንዲያሳዩ ማድረግና ተሳትፎዋቸውን እየጨመሩ እንዲሄዱ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ በምልከታው እንደ ተገለጸው መምህሩ የንግግር ትምህረት በሚያስተምሩበት ወቅት የተለያዩ ንግግርን የሚያሣድጉ ተግባራትን ቢያከኛውኑም ግማሹን ደግሞ ሳይተገብሩት በግዴለሽነት አልፈውታል፡፡ የተለያዩ ትምህረቱን ለመተግበር የሚረዱ ተግባራት በመማሪያ መጽፉ ላይ ቢገኙም መልመጃዎቹን ተማሪዎችን አሰርቶ በተግባር እንዲያሳዩ ከማድረግ ይልቅ መምህሩ እራሱ ሰርቶ በራሱ በመፈጸም የሚያከናውኑበት ሁኔታ ታይቷል፡፡ ይህ ደግሞ የንግግር ትምህርት የታለመለትን ሁኔታ ከግብ እንዳይ ደርስ እንቅፋት ይሆናል፡፡

መምህራን የንግግር ትምህርትን በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎች በደንብ እንዲሳተፉና ተሳትፎዋቸው ከግዜ ወደ ጊዜ እንዲጨምር ማድረግ አለባቸው፡፡ የተማሪዎች ተሳትፎ የሌለው የንግግር ትምህርት ውጤታማነቱ በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በምልከታው እንደ ተገለጸው መምህራን የዕለቱን የንግግር ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት የመማር ማስተማር ሂደት ላይ ተማሪዎቹን ያሳተፉት 1 (25%) ሲሆኑ ያላሳተፉት ደግሞ 3 (75%) ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው መምህሩ በክፍል ውስጥ የሚደረዱ ማንኛውንም የመማር

ማስተማር ተግባር እራሱ ተግብሮ እንደሚጨርሰው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን እንዳያሳድጉ ትልቅ ችግር ይሆንባቸዋል፡፡

አንድ መምህር በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ተግባርን በሚያከናውንበት ወቅት የተለያዩ ባህሪ ያላቸው ተማሪዎችን እንደሚያስተምር ማወቅ ይኖርበታል፡፡ የነዚህተማሪዎች ባህሪም በውስጣቸው ያለውን እውቀት አውጥተው መናገር የሚፈሩ፣ በሰው ፊት መናገር የሚያስፈራቸውና በፍጹም ሰው ፊት ቆመው የመናገር ልምድ የሌላቸው ናቸው፡፡ስለዚህ መምህራን እነዚህን ተማሪዎች ባህሪያቸውን አውቀው በክፍል ውስጥ ሳይፈሩ እንዲሳተፉ ማበረታታት ይኖርባቸዋል፡፡ ur (1996) እንደገለጹት በልምምድ ወቅት ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች የመናገር ችግር ከሚያጋጥማቸው መካከል ዋና ዋናዎቹ መታቀብ፣ የሚናገሩትን ነገር ማጣትና ዝቅተኛ ወይም ሁሉን ያላማከለ ተሳትፎ ማድረግ ነው፡፡

ከላይ በምልከታው እንደተገለጸው የንግግር ትምህርትን በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ወቅት መምህራን የእለት ትምህርታቸውን ሲያከናውኑ የመፍራትና የመናገር ልምድ የሌላቸውን ተማሪዎች ያበረታቱ 4 (100%) ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው መምራኑ ተማሪዎች ያላቸውን ዕውቀት ወይም የንግግር ችሎታ በፍርሃት ምክንያት ሳይናገሩና ሳያወጡት እንዳይቀሩና በተቃራኒው ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውንና የንግግር እውቀታቸውን እንዲያካብቱ ያስችላቸዋል፡፡

አንድ መምህር የንግግር ትምህርትን ክፍል ውስጥ በሚያከናውንበት ወቅት ተማሪዎችን ማሳተፍና ሁሉም ተማሪዎች የላቀ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉ ማድረግ አለበት፡፡ ተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህረት በሚያከናውበት የክፍል ውስጥ ልምምድ በሚደረግበት ወቅት እንዲሳተፉ ማስቻለና ድርጊቱን ሁሉም ተማሪዎች እንዲተገብሩ ማድረግ የመምህሩ የማይተካ ሚና ነው፡፡ ከዚህ በመነሳት በምልከታው ቅጽ እንደ ተመለከትነው መምህራን የእለት ትምህርታቸውን ሲያከናውኑ በንግግር ትምህርት ልምምድ ወቅት ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን እንዲያከናውኑ ያደረጉት 1 (25%) ሲሆኑ ያላደረጉት ደግሞ 3 (75%)ናቸው፡፡ ይህ የሚያሣየው ብዙ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርትን በሚያስተምሩበት ጊዜ ተማሪዎች የንግግር ተግባራትን እንዲያከናውኑ አያደርጓቸውም ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪዎች የንግግር ትምህርትን በሚገባ ለማግኘትያሥቸግራል፡፡

የንግግር ክሂል ትምህረት በምናከናውንበት ወቅት በግል ወይም በተናጥል ተሳትፎ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በቡድን መወያየትም ንግግር ተግባር ማከናወኛ መንገድ ነው፡፡ መምህራን የንግግር ትምህርትን በሚተገብሩበት ወቅት ተማሪዎች ተማሪዎች የሚሰሩትን የንግግር ተግባር እርስ በርስ እንዲወያዩና የመወያየት ባህል እንዲኖራቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በምልከታ በተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው መምህራን የእለት ትምህርታቸውን ሲያከናውኑ ተማሪዎች በልምምድ ወቅት እርስ በርስ የመወያየት ባህሪ እንዲኖራቸው

ያደረጉት 2 (50%) ሲሆን ያላደረጉት ደግሞ  2 (50%) ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው መምህራን የንግግር ትምህርት በሚያስተምሩበት ወቅት ግማሾቹ እረስ በርስ የመወያየት ባህሪ እንዲኖራቸው ያደረጉት ሲሆን ገሚሶቹ ደግሞ አላደረጉም፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርት በሚገባ እንዲያሳድጉ አያስችላቸውም፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች የራሳቸውን የአነጋገር ስልት በመጠቀምና የንግግር ክሂል አተገባበር ሂደት ጋር በማስማማት እንዲተገበሩ መምህራን የራሳቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው፡፡ ተማሪዎችም የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ ሲተገበር ሁሉም እንዲሳተፉ፣ የመናገር ችሎታ የሌላቸውን ማበረታታት፣ የንግግር ተግባሩን እንዲያከናውኑ ማድረግና እርስ በርስ የመወያየት ባህል እንዲኖራቸው ማድረግ የመምህራን ሚና ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች የንግግር ክሂልን በራሳቸው የቃላት አጠቃቀም ና የሰዋሰው አጠቃቀም እንዲጠቀሙና የክፍል ተሳትፎዋቸውን እንዲያጎለብቱ ማስቻል አለባቸው፡፡

*4.1.1.4. ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽ እንዲችሉ የመምህሩን ሚና የሚያሳይ*

**ትንተና**

Byme (1986: 55) እንደገለጸው መምህራን የንግግር ክሂል ትምህረት ተግባራትን በሚያስተምሩበት ጊዜ ተግባራቱ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታቸውን የሚያሳድጉና ሀሳባቸውን በነፃነት የሚገልፁባቸው መሆን አለባቸው፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህረትን በክፊል ውስጥ በሚተገበሩበት ወቅት በተረዱትና እነሱ በገባቸው መንገድ ሀሳባባቸውን በነፃነት እንዲገልፁ ማስቻል የመምህራን አይተኬ ሚና ነው፡፡ ተማሪዎችም የንግግር ክሂል ትምህርትን እነሱ በገባቸው ና በተረዱት መንገድ ከራሳቸው የህይወት ገጠመኞች ጋር በማያያዝ በነፃነት መግለፅ አለባቸው፡፡

**ሰንጠረዥ 4. የንግግር ክሂል ትምህርት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽ እንዲችሉ የመምህሩ ሚና የሚያሳይ መግለጫ**

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘዴ ትግበራ ጥያቄዎች | አማራጮች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎ | | አይደለም | |
| | | በቁጥር | በፐርሰንት | በቁጥር | በፐርሰንት |
| 16 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ እርምት ለመስጠት ጥረት ተደርጓል? | 4 | 100% | ---- | ------ |
| 17 | የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉና በነጻነት ሃሳባቸውን መግለጽ የሚችሉበት ሁኔታ የተከናወኑ ናቸው? | 2 | 50% | 2 | 50% |
| 18 | ስዕሎችና ፎቶግራፎችን ክፍል ውስጥ በማቅረብ በንግግር መልክ ዕንዲያቀርቡ ተደርጎዋል? | ----- | ------ | 4 | 100% |

በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት መምህራን የንግግር ተገባር ሲያከናውኑ ተማሪዎች በልምምድ ወቅት የተለየዩ ስህተቶችን ሲፈጥሩ እርምት መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎችም የተሰጣቸውን እርምት በመቀበልና በማስተካከል የንግግር ክሂል ተግባራቸውን በሚገባ ማከናወን አስፈላጊው ተግባር ነው፡፡ መምህራንም እርምት በሚሰጡበት ወቅት የተማሪዎቹን ስነ ልቦና በማይጎዳና ሊያበረታታቸው በሚችል መልኩ ቢሆን የተመረጠ ነው፡፡ ለተማሪዎች እርምት በሚሰጥበት ወቅት የሚያሰሽማቅቅና ስነልቦንቻውን የሚነካ ከሆነ ተማሪዎች ለንግግር ትምህርት የሚኖራቸው ፍላጎት በጣም ዝቅተኛ ይሆናል፡፡

ስለዚህ መምህራን የንግግር ክሂል ትምህረትን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ተማሪዎች ሲሳሳቱ ተገቢ በሆነ መንገድ ስተቱን ማረም ይኖርባቸዋል፡፡

በምልከታ ቅጹ ላይ እንደተመለከትነው መምህራን የዕለት የክፍል የንግግር ትምህርታቸው ውስጥ በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ እርምት የሰጡት 4 (100%) ናቸው፡፡ ይህም ማለት ሁሉም መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን ክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ወቅት በአግባቡ ስህተታቸውን ለማስተካከል ሞክረዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የንግግር ትምህርትን በሚተገበሩበት ወቅት የተለያዩ ስህተቶችን ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የፈጠሩትን የተለያዩ ስህተቶች ደግሞ መምህራን ተማሪዎቹን በማያስደነግጥና በማያስፈራ እንዲሁም በሚያበረታታቸው መንገድ እርምት የመስጠት ሀላፊነት አለባቸው፡፡

መምህራን አንድን የንግግር ትምህረት በሚያስተምሩበት ጊዜ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በሚገባ እነሱ ትምህርቱን በተረዱትና በተገነዘቡት መንገድ ከራሳቸው የህይወት ገጠመኞች ጋር በማያያዝ በነጻነት መግለጽ እነዲችሉ ማድረግ አለባቸው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎች በሚማሩት የንግግር ትምህርት ዙሪያ ምን ተረዱ፣ ያላቸውስ እውቀት ምን ይመስላል፣ ከራሳቸው የህይወት ገጠመኞች ጋርስ እንዴት አያይዘው ማውረብ ይችላሉ የሚሉ ሀሳቦችን በማገናዘብ መምህራን ተማሪዎች ሃሳባቸውን በነጻነት እነዲገልጹ ማድረግ ከፍተኛ ሚናቸው ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችም በንግግር ትምህርት ጊዜ የራሳቸውን ሀሳብ ያለምንም ፍራቻ የተገነዘቡትንና የተረዱትን ነገር በነጻነት መግለጽ ይኖርባቸዋል፡፡

በሰንጠረዡ ውስጥ እንደ ተገለጸው በምልከታ የተገኘውን መረጃ ስንመለከት መምህራን የንግግር ትምህርትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ሲያደርጉ በንግግር ልምምድ በቀላሉና በነጻነት ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ያደረጉት 2 (50%) ሲሆኑ በነጻነት ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ያላደረጉት ደግሞ 2 (50%) ናቸው፡፡ ከዚህ የምንረዳው የተወሰኑ መምህራን ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እነዲገልጹ ሲያደርጉ ሌሎች አላደረጉም ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች በእኩል ደረጃ የንግግር ትምህርትን እንዲያውቁና ስለ ንግግር ትምህርት የተሻለ እውቀት እነዲኖራቸው አያደርግም፡፡

Harmer (2007) እንደ ገለጹት ተማሪዎች በቡድን ይቀመጣሉ ለእያንዳንዱ ቡድን ተከታታይነት ያላቸውን መልእክት አዘል ስእሎች ይሰጣል፤ በቡድኖቹ ስእሎቹን ከተመለከቷቸው በኋላ ስእሎቹ ይሰበሰባሉ፤ ከዚያም ከመጀመሪያዎቹ ቡድኖች አንድ አንድ አባል የያዙ ሌሎች አዳዲስ ቡድኖች ይደራጃሉ፡፡ አዲሶቹ ቡድኖችም ቀደም ሲል ያዩት ስእላዊ መግለጫ ምን መልእክት እነደሚያስተላልፍ ይናገራሉ፡፡ በመጨረሻም በእያንዳንዱ ቡድን የቀረበው ታሪክ ተመሳሳይ ሀሳብ የያዘ መሆኑንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ ቡድኖች የየራሳቸውን ታሪክ ለክፍል ያቀርባሉ፡፡ ተግባራቱ የሚቀርብበት ጊዜም የሚቀርበው ተግባራት ለተገልጋዮች ህይወት ቅረበት ያላቸው መሆን እንደሚገባቸው ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ እንደምንረዳው የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በምንተገብርበት ወቅት የንግግር ልምምድን ተግበራዊ ስናደርግ የተለያዩ ፎቶግራፎችና ስዕሎችንም የምንጠቀም ከሆነ የተሻለ እውቀት ልናስጨብጥ እንችላለን፡፡

ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ በምልከታ ቅጽ ላይ እንደ ተገለጸው መምህራን የእለት ትምህርታቸው ውስጥ የንግግር ትምህርትን ሲተገብሩ የንግግር ልምምድ ላይ ፎቶ ግራፎችና ስእሎችን በማቅረብ ተማሪዎች ንግግር እንዲያቀርቡ ያደረጉት የሉም፡፡ ሁሉም መምህራን መጽሀፉ ላይ ያለውን ብቻ በመናገር በራሳቸው ሃሳብ የንግግር ትምህረቱን በሀሳብ ብቻ ገልጸው ያልፉታል፡፡ ይህ ደግሞ የንግግር ትምህርት የታለመለትን ግብ እንዳይመታ ያደርገዋል፡፡

በአጠቃላይ በምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ተግባርን በሚተገብሩበት ወቅት ተማሪዎች ልምምዶችን ሲያከናውኑ የተለያዩ መተግበሪያዎችን እዲያከናውኑ ቢደረጉም ተማሪዎች የመተገበር ፍቃደኝነት እንደሌላቸው ተመልክተናል፡፡ መምህራኖችም ተግባራቱን ስራ ላይ በሚያዉሉበት ጊዜ የተወሰኑትን መተግበሪያ መንገዶች እንደማይጠቀሙ ተገንዝበናል፡፡

### 4.1.2. ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ የንግግር ክሂል አተገባበር የተማሪዎች ምላሽ

#### *4.1.2.1. መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት* **የሚተገበሩ ተግባራት ትንተና**

መምህራን የንግግር ትምህርትን ከማከናቸው በፊት የተለያዩ ተግባራትን ተማሪዎች እነዲያከናውኑ ያደርጋሉ፡፡ ተማሪዎችም እነዚህን ተግባራት ከመምህራኖቻቸው በመቀበል በክፍል ውስጥና በቤታቸው ይዘው በመግባት የተለያዩ ልምምዶችን በማድረግና የንግግር አቅማቸውን በማጎልበት በክፍል ውስጥተግባራቱን ያከናውናሉ፡፡ መምህራንም ይህን ተግባር እውን ለማድረግ ወደ እለቱ ትምህርት ከመግባታቸው በፊት የተለያዩ ነገሮችን ተማሪዎች እንዲተገብሩና ለእለቱ ትምህርት ማግቢያ ወይም አጋዥ የሆኑ ነገሮችን እንዲተገብሩ ያደርጋሉ፡፡

**ሰንጠረዥ 5. የንግግር ክሂል ተግባራትን አቀራረብን የተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ**

**መስጫ መግለጫ**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የንግግር ትምህርት ተግባራዊ ከማድረጋቸው በፊት አላማውን በግልጽ ይነግራችኋል? | 44 | 73.3% | 14 | 23.3% | 2 | 3.3% | | |
| 2 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንግግር ትምህርት ወቅት የመከታተል ፍላጎት አለህ/አለሽ? | 5 | 8.3% | 41 | 68.3% | 14 | 23.3% | | |
| 3 | የንግግር ትምህርት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት መምህራን ማነቃቅያዎችን ያቀርባሉ? | 39 | 65% | 17 | 28.3% | 4 | 6.6% | | |
| 4 | የአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ክሂል መተግበሪያ ክፍሎች የንግግር ክሂልን ለማዳበር ይጠቅማሉ? | 55 | 91.6% | 5 | 8.3% | | | | |
| 5 | በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት ምን ያህል ተሳትፎ ታደርጊያለሽ/ህ? | 19 | 31.6% | 22 | 36.6% | 19 | 31.6% | | |
| 6 | መምህሩ የንግግር ክሂል ተግባር ከመጀመሯ/ሩ በፊት አጠር ያለ መመሪያ ይሰጣሉ? | 22 | 36.6% | 38 | 63.3% | | | | |
| 7 | ተማሪዎች የንግግር ተግባር ከማከናወናቸው በፊት ምሳሌ ይሰጧችኋል? | 13 | 21.6% | 11 | 18.3% | 36 | 60% | | |

ከላይ በቀረበው ሰነጠረዥ ውስጥ እንደተገለጸው በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል በሚቀርብበት ወቅት ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎች የተለያዩ መላሶችን ሰጥተዋል፡፡ እነዚህም መልሶች በክፍል ውስጥ የሚከወኑ የንግግር ክሂል የመምህራንን የአተገባበር ሁኔታ የሚያሳየን ነው፡፡ ስለሆነም የተማሪዎችን መልስ ስንመለከት የንግግር ትምህርትን ተግባራዊ ከማድረጋቸው በፊት አላማውን በግልጽ ተነግሯችኋል ተብለው ሲጠየቁ 13 (23.3%) ተማሪዎች አንድ አንድ ጊዜ ይነግሩናል ብለው ሲመልሱ፤ 2 (3.3%) አልፎ አልፎ ይነግረናል ያሉ ሲሆን፤ 44 (73.3%) ብዙ ጊዜ ይነግረናል በማለት መልሰዋል፡፡

ከዚህ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ የምንረዳው መምህራን የዕለቱን ትምህርት ከማቅረባቸው በፊት የትምህርቱን አላማ እንደሚገልጹላቸው ብዙ ተማሪዎች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡፡ የተወሰኑ ተማሪዎች እንደመለሱት ደግሞ አንድ መምህር አላማውን እንደማይገልጽላቸው ከተገኘው መረጃ ማወቅ ይቻላል፡፡

በማስከተልም ተማሪዎች ከሞሉት መጠይቅ መረዳት እንደሚቻለው በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት የመከታተል ፍላጎት አለህ/አለሽ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 5 (8.3%) ፍላጎታቸው ከፍተኛ እንደሆነ ሲገልጹ፤ 41 (68.3%) ደግሞ ፍላጎታቸው በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ሲመልሱ፤ 14 (23.3%)ፍላጎታቸው መካከለኛ እንደሆነ በምላሹ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል ትምህርትን ለመከታተል ብዙ ተማሪዎች ፍላጎ እንዳላቸው ነው፡፡ ጥቂት ተማሪዎች ደግሞ በመጠኑም ቢሆን እንደሚከታተሉና ፍላጎታቸው አነስተኛ እንደ ሆነ ከመጠይቁ ምላሽ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ሆኖም መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በሚተገብሩበት ወቅት ከተማሪዎች ከተገኘው በመጠይቁ ላይ በተሞላው መልስ እንደምንረዳው የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት መምህራን ማነቃቅያዎችን ያቀርባሉ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 39 (65%) የሚሆኑ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ያነቃቁናል በማለት ሲመልሱ፤ 17 (28.3%) አንድ አንድ ጊዜ ያነቃቃሉ በማለት መልስ ሲሰጡ 4 (6.6%) የሚሆኑት ደግሞ አልፎ አልፎ ያነቃቃሉ በማለት በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ይህ ሀሳብ እንደሚያመለክተው የንግግር ክሂል ትምህርትን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት ብዙ መምህራኖች ማነቃቅያ ለተማሪዎች እንደሚሰጡና አንድ አንድ አንድ መምህራን ደግሞ ማነቃቅያን ሲያሰኛቸው ብቻ እንደሚሰጡ ከመጠይቁ መልስ መረዳት ይቻላል፡፡

የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት ለተማሪዎች ለቀረበው የጽሁፍ መጠይቅ የተሰጠውን መልስ በሰንጠረዡ ውስጥ የተገለጸውን መረጃ ስንመለከት እንደሚከተለው ተገልጾዋል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ክሂል መተግበሪያ ክፍሎች የንግግር ክሂልን ለማዳበር ይጠቅማሉ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 55 (91.6%) በጣም ይጠቅማል ሲሉ 5 (8.3%) ደግሞ በመጠኑም ቢሆን ይጠቅማል በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው አማርኛ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ክሂል መተግበሪያ ክፍሎች የንግግር ክሂልን ለማዳበር ጠቀሜታው የላቀ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የንግግር ቋንቋ በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ያለውን የንግግር ክሂል መተግበሪያዎችን ብቻ ተጠቅሞ ከክፍል መውጣት ሳይሆን ተማሪዎችንም ባሳተፈ ሁኔታ መልኩ መተግበር ያስ ፈልጋል፡፡

ይህም ሲባል በንግግር ክሂል ትምህርት ጊዜ የተማሪዎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ ያሥፈልጋል፡፡ በመጠይቁ መልስ ላይ የቀረበውን የተማሪዎች መልስ ሲንመለከት በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት ምን ያህል ተሳትፎ ታደርጊያለሽ/ህ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 19 (31.6) የሆኑ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ እሳተፋለው ፤ 22 (36.6) የሆኑት ደግሞ መምህሩ ሲጠይቀኝ ብቻ እሳተፋለው ሲሉ፤ 19 (31.6)የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ አልፎ አልፎ እሳተፋለው በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ጥቂት ተማሪዎች የመሳተፍ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ቢሆንም የተቀሩት ደግሞ በጠቂቱም ቢሆን እንደሚሳተፉ የተሰጠው የመጠይቁ መልስ ያመለክታል፡፡

ስለሆነም ተማሪዎች ከሞሉት መጠይቅ መረዳት የሚቻለው የንግግር ክሂል ተግባራት ከመቅረባቸው በፊት መምህሩ አጠር ያለ መመሪያ ይሰጣሉ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 22 (36.6%) የሆኑት ተማሪዎች አንድ አንዴ ይሰጣሉ ሲሉ፤ 38 (63.3%) የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ብዙ ጊዜ ይሰጣሉ በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ ሀሳብ የሚያመለክተው አንድ አንድ መምህራን ግልጽ የሆነ መመሪያ እንደሚሰጡና አንድ አንዶች ደግሞ እንደሚፈልጉት አድርገው በፈለጋቸው ሰአት መመሪያ እንደሚሰጡ የመጠይቁ መልስ ያመለክታል፡፡

እንዲሁም የንግግር ክሂል ተግባርን በተመለከተ ለተማሪዎች የቀረበውን መጠይቅ አስመልክቶ የተሰጠውን ምላሽ ስንመለከት ተማሪዎች የንግግር ክሂል ተግባር ከማከናወናቸው በፊት ምሳሌ ይሰጧቸዋል ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 13 (21.6%) የሆኑ ተማሪዎች አንድ አንዴ ይሰጣሉ፤ 11 (18.3%) የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ አልፎ አልፎ ይሰጣሉ ሲሉ፤ 36 (60%) የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ብዙ ጊዜ ይሰጣሉ በማለት መልሳቸውን አስፍረዋል፡፡ ይህ ሀሳብ የሚያሳየው ብዙ መምህራን የንግግር ትምህርትን ተማሪዎች ከማከናወናቸው በፊት ምሳሌ እንደሚሰጧቸውና አንድ አንድ መምህራንደሞ እንደማይ በፈለጉት ጊዜ ብቻ እንደሚሰጧቸው ከቃለመጠቁ ላይ የተሰጠው ምላሽ የመለከታል፡፡

በአጠቃላይ መምህራን የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ከማከናወናቸው በፊት አላማን ግልጽ ማድረግ፤ ማነቃቅያ መስጠት፤ አጠር ያለመመሪያ መስጠትና ምሳሌዎችን ለተማሪዎች በመስጠት ሁኔታ ላይ ብዙ የተወሰኑ መምህራን በብዛት እንደሚተገብሩትና ጥቂት የሆኑ መምህራን ደግሞ በጥቂቱ እንደሚተገብሩት መረዳት ተችሎዋል፡፡

*4.1.2.2. የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ የላቸውን የማሪዎች ተሳትፎ በተመለከተ*
**ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ትንተና**

የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት መምህራን የተማሪዎችን ተሳትፎ ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የተማሪዎች ተሳትፎም በክፍል ውስጥና በተለያዩ

ቦታዎች ላይ የንግግር ስራዎችን በመስጠት የተማሩትን የንግግር ተግባር ከራሳቸው ገጠመኝና የህይወት ክስተቶች ግር በማያያዝ እንዲያቀርቡና ተሳትፎዋቸውን እንዲያጎለብቱ ማድረግ የመምህራን ሚና ነው፡፡ ይህም በሚደረግበት ጊዜ መምህራን የተማሪዎቹን የንግግር ክሂል አተገባበርቸውን መከታተል ያስፈልጋል፡፡

**ሰንጠረዥ 6. የንግግር ክሂል ተግባራትን የተማሪዎች ተሳትፎን የተመለከተ የተማሪዎች**

**ምላሽ መስጫ መግለጫ**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 8 | መምህሩ የንግግር ክሂል ትምህርትን በሚተገብሩበት ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የመሳተፍ እድል ይሰጣሉ? | 14 | 23.3% | 19 | 31.6% | 19 | 31.6% | 8 | 13.3% |
| 9 | በግልና በቡድን ውይይትና ክርክር በአንድነት በመሆን የንግግር ክሂልን የመተግበር ሁኔታ በክፍል ውስጥ ነበር? | 33 | 55 % | 16 | 26.6% | 8 | 13.3% | 3 | 5 % |
| 10 | በግልና በቡድን የንግግር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት መምህሩ እየተከታተሉ ያበረታታሉ? | 16 | 26.6% | 3 | 5 % | 38 | 63.3% | 3 | 5 % |
| 11 | ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎችን በራስ መተማመን እንዲኖራቸው የማበረታታት ሂደቱ እንዴት ያለ ነው? | 27 | 45 % | 8 | 13.3% | 25 | 41.6% | | |
| 12 | የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ ለመተግበር የክፍል ሁኔታ እንዴት ያለ ነው? | 19 | 31.6% | 19 | 31.6% | 22 | 36.6% | | |

የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ ተማሪዎች በተለያዩ ሁኔታዎች በክፍል ውስጥ መሳተፍ ማስቻል አስፈላጊ ነው፡፡ ስለሆነም ተማሪዎችም የንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ና የሚማሩትን የንግግር ክሂል ትምህርት በተግባር እንዲተገብሩት ማድረግ የመመምህሩ ከፍተኛ ሚና ነው፡፡ይህን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በመጠይቁ ላይ መምህሩ የንግግር ክሂል ትምህርትን በሚማሩበት ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የመሳተፍ እድል ይሰጣሉ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 14 (23.3%) ተማሪዎች ብዙ ጊዜ እድል ይሰጣሉ፣ 19 (31.6%) ተማሪዎች አንድ አንድ ጊዜ እድል ይሰጣሉ፣ 19 (31.6%) ተማሪዎች ሁል ጊዜ እድል ይሰጣሉ፣8 (13.3%) በፍጹም እድል አይሰጡም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚገልጸው ብዙ መምህራን እንደየሁኔታው ለንግግር ትምህርት ተግባር ለተማሪዎች ተሳትፎ እድል ሲሰጡ ጠቂት መምህራን ግን ለተማሪዎች ተሳትፎ ትኩረት እንደማይሰጡና እንደማያሳትፏቸው የተገኘው የተማሪዎች መልስ ያመለክታል፡፡

ከላይ በሰንጠረዡ ውስጥ እንደተገለጸው የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እንዲያደርጉት በሚደረግበት ወቅት ተማሪዎች ንግግርን በተግባር እንዲያከናወኑ ሲደረግ የተለያዩ ንግግሮችን፣ ክክሮችን፣ ጭውውቶችን፣ ውይይቶችን ወዘተ--- በሚያደርጉበት ጊዜ ሀሳባቸውን ማቀናጀት፣ ማደራጀትና ንግግርን ተለማምደው የንግግርን ስረአት እንዲገነዘቡ ለማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪዎችም የሚቀርብላቸውን የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ማቅረባቸውን ና የጭውውት፣ የክርክር፣ የውይይት ወዘተ ተግባራትን ለማከናወን እንደ ረዳቸው መመልከት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በመጠይቁ ላይ እንደቀረበው ተማሪዎች በግልና በቡድን ውይይትና ክርክር በአንድነት በመሆን የንግግር ክሂልን የመተግበር ሁኔታ በክፍል ውስጥ ነበር ተብለው ሲጠየቁ የመለሱት መልስ 33 (55%) የሚሆኑ ተማሪዎች አንድ አንድ ጊዜ አለ፣ 16 (26.6%) የሚሆኑ ተማሪዎች አልፎ

አልፎ አለ፣ 8 (13.3%) የሚሆኑ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ አለ፣ 3 (5%) የሚሆኑት ተማሪዎች ምንም የለም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው ብዙ መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ወቅት ተማሪዎች በጥንድና የቡድን ስራዎችን በአንድነት እንዲተገብሩ ያደረጉ ሲሆን፤ ሌሎች ጥቂት መምህራን ደግሞ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር የቡድንና የጥንድ ስራዎችን ተግባራዊ እንማያስደርጓቸው ከተሰጠው መልስ መረዳት ይቻላል፡፡

ሆኖም የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት መምህራን ለተማሪዎች የተለያዩ የግለ፣ የጥንድና የቡድን ስራዎችን እንዲያከናወኑ መስጠትና በጥሞና መከታተል ብቻ ሳይሆን በራስመተማመናቸው እንዲጨምር ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ ይህ በሚደረግበት ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ በግልና በጥንድ እንዲሁም በቡድን የሚሰጣቸውን ተግባር በመየከናወኑበት ወቅት ከሚተገብሩት ነገር የንግግ አተገባበርን መገንዘብ መቻላቸውን ለመከታተል ያስችላል፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ በመጠይቁ ላይ ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን የንግግር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት መምህሩ እየተከታተሉ ያበረታታሉ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 16 (26.6%) የሆኑት ተማሪዎች አንድ አንዴ ያበረታታሉ፣ 3 (5%) የሆኑ ተማሪዎች አልፎ አልፎ ያበረታታሉ፣ 38 (63.3%) የሆኑ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ያበረታታሉ፣ 3 (5%) የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ምንም አያበረታቱም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ሃሳብ እንደሚያመለክተው ብዙ መምህራን የንግግር ክሂል ተግባርን በሚያከናወኑበት ጊዜ ተማሪዎችን የማበረታታ ስራ ቢሰሩም ጥቂት መምህራን ግን ይህን ተግባር እንደ ዘነጉት ያሳየናል፡፡

በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ተግባር በሚተገበርበት ጊዜ ተማሪዎች ለላቀ ተሳትፎ ማድረግ እንዲችሉ ማድረግ የመምህሩ ስራ ነው፡፡ ይህም ሲባል የንግግር ክሂል ተግባራዊነት በክፍል ውስጥ መገለጽ የሚቻለው በታማሪዎች ተሳትፎ ስለሆነ ነው፡፡ መምህራንም የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የተለያዩ ባህሪያን ለመናገር የመፍራትና በራስ መተማመን የሌላቸው ተማሪዎችን የንግግር ተግባሩን እንዲሰሩ የማድግና የማበታታት ስራ መስራት ዋነኛ ተግባር ነው፡፡ ይህን መነሻ በማድረግ ተማሪዎች ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎችን በራስ መተማመን እንዲኖራቸው የማበረታታት ሂደቱ እንዴት ያለ ነው ተብለው ሲጠየቁ የመለሱት መልስ 27 (45%) የሆኑ ተማሪዎች በጣም ጥሩ ነው፣ 8 (13.3%) የሆኑ ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ ነው፣ 25 (41.6%) የሆኑት ተማሪዎች ደግሞ መካከለኛ ነው በማለት መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ መጠይቅ የምንረዳው የንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት ለመናገር የሚፈሩትን ተማሪዎች በራስ መተማመናቸው እንዲጨምር የሚያበረታቱ መምህራን ሁሉም ናቸው በማለት መልሰዋል፡፡

የነግግር ክሂል በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት መምህራን የክፍሉን ሁኔታ በተቻለ መጠን ተማሪዎችን የሚስብና እንደልባቸው ሳይጨናነቁ ሀሳባቸውን የሚገልጹበት

መሆን ይኖርበታል፡፡ ተማሪዎችም የንግግር ክሂል ትምህርትን በሚማሩበት ወቅት የክፍሉ ሁኔታ ምቹ ና እንደልባቸው ሀሳባቸውን ለመግለጽ የማያጨናንቃቸው ከሆነ የንግግር ተግባሩን ለማከናወን ሁነኛ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች መጠይቁ በቀረበው መሰረት የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ ለመተግበር የክፍሉ ሁላታ እንዴት ያለ ነው ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 19 (31.6%) የሆኑ ተማሪዎች የክፍሉ ሁኔታ ምቹ ሁኔታ አለው፣ 19 (31.6%) የሁኑት ተማሪዎች የክፍሉ ሁኔታ በመጠኑም ምቹ ነው፣ 22 (36.6%) የሆኑት ተማሪዎች የክፍሉ ሁኔታ በጣም ምቹ ነው በማለት ምላሻቸው ሰጠተዋል፡፡ በዚህ ሀሳብ ውስጥ እንደምንረዳው የንግግር ተግባርን በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት የክፍሉ ሁኔታ ምቹ እንደሆነና በተወሰነ ሁኔታ አንዳድ ክፍል ላይ አነስ ያለ ጉድለት እንዳለው ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የንግግር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ መምህራን ሲተገብሩ የተለያዩ መተግበሪያ ወይም ማከናወኛ ተግባራትን ውይይት፣ ጭውውት፣ ክርክር ወዘተ ሌሎችን ያከናወን ሲሆን ተማሪዎችንም በራስ መተማመናቸው እንዲጎለብት ብዙ መምህራን የማበረታታት ስራን ተግባራዊ እንዳደረጉ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

*4.1.2.3. የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ያላቸውን የተማሪዎች ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ በተመለከተ ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ ትንተና*

የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ በሚከወንበት ወቅት መምህራን የተለያዩ ተግባራትን እንዲከውኑ ተማሪዎቻቸውን ማስቻል ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎች የንግግር ክሂል ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ተማሪዎች በተለያዩ የልምምድ ወቅት ያገኙትን እውቀትና ግንዛቤ በክፍል ውስጥ በነጻነት እንዲገልጹ ማድረግ የመምህራን ከፍተኛ ተግባር ነው፡፡ የንግግር ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የተለያዩ ስራዎችን በቡድንና በጥንድ እንዲሰሩ በማበረታታትና ስህተት ሲፈጥሩ በመከታተል ስህተታቸውን በማረም የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ችሎታቸውን ማዳበር እንዲችሉ ማድረግ የመመምር ሚና ነው፡፡

**ሰንጠረዥ 7. የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ሀሳብን በነጻነት መግለጽን**

**የተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ መ**

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 13 | የንግግር ተግባርን በምታከናውኑበት ጊዜ ሀሳባችሁን በነጻነት እንድትገለጹ መምህሩ ያደርጋችኋል? | 19 | 31.6% | 27 | 45% | 14 | 23.3% | | | | |
| 14 | በክፍል ውስጥ በጭውውት፣ በክርክርና በውይይት መሰል ተግባራትን እንዲለማመዱና የንግግር ችሎታን እንዲያጎለብቱ ተደርጓል? | 25 | 41.6% | 17 | 28.3% | 8 | 13.3% | 5 | 8.3% | 5 | 8.3% |
| 15 | በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት ስህተት ሲፈጠር ቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስ በርስ እንዲተራረሙ ይደረጋል? | 23 | 38.3% | 19 | 31.6% | 10 | 16.6% | 8 | 13.3% | | |
| 16 | መምህሩ የተለያዩ ስልቶችን፣ ፎቶግራፎችን ቅርጻቅርጾች በክፍል ውስጥ አምጥቶ ተማሪዎች እንዲነጋገሩበት በማድረግ ሁኔታ ምን ይመስላል? | 11 | 18.3% | 14 | 23.3% | 2 | 3.3% | 13 | 21.6% | 20 | 33.3% |

Harmer (1991:105) እንደገለጸው ንግግርን ለማስተማር ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው በተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች ተማሪዎች አስቀድመው ተዘጋጅተው ወይም ተለማምደው ውይይት ወይም ክርክር በማድረግ ሁሉም ተማሪዎች በሚያሳትፍ

መልኩ ሲቀርብ ነው፡፡ ተማሪዎች በተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንዲወያዩ፣ እነዲለማመዱና በቋንቋው ተጠቅመው ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ መምህራን እንዲያበረታቱ ይመረጣል፡፡

ከላይ በስንጠረዡ ውስጥ እንደተገለጸው የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት መምህራን ተማሪዎችን ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ማስቻል ይኖርባቸዋል፡፡ይህም ማለት ተማሪዎች የንግግር ተግባርን በክፍል ውስጥ ለማከናወን ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት ያገኙትን እውቀት ወይም ልምድ ያለምንም ፍረሀት በነጻነት ሀሳባቸውን መግለጽ እንዲችሉ ማድረግ የመምህራን ሚና ነው፡፡ ይህን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ተማረዎች የንግግር ተግባርን በምትከናውኑበት ጊዜ ሀሳባችሁን በነጻነት እንድት ገልጹ መምህሩ ያደርጓችኋል ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 19 (31.6%) የሆኑት ተማሪዎች በጣም ጥሩ ነው፣ 27 (45%) የሆኑት ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ ነው፣ 14 (23.3%) የሆኑት ተማሪዎች ደግሞ መካከለኛ ነው በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዘህ የምንረዳው ጥቂት መምህራን የንግግር ክሂል ተግባር ላይ ተማሪዎች በነጻነት ሀሳባቸውን እንዲገልጹ በማድረጉ ሂደት ላይ ብዙም ትኩረት ባይሰጡም ብዙ መምህራን ግን ተማሪዎች በነጻነት ሀሳባቸውን እንዲገለጹ አድርጓቸዋል፡፡

ሆኖም የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በሚተገበሩበት ጊዜ መምህራን ተግባራቱን ለማከናወን እና ስራ ላይ በማዋል ተማሪዎች የተለያዩ ውይይቶች፣ ክርክሮችና ጭውውቶችን እንዲተገበሩ ማድረግ የንግግር ክሂል ተግባርን ለመተግበር ልምድና ክህሎት እንዲያዳብሩ ያስችላል፡፡ ተማሪዎችም ዕነዚህን የንግግር ክሂል መተግበሪያ ሁኔታዎችን በማከንወን ያገኘውን ልምድን ያካበተውን ችሎታ እንዲያንጸባረቅ ያስችላቸዋል፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች በመጠይቁ ላይ በክፍል ውስጥ በጭውውት፣ በክርክርና በውይይት መልክ ተግባራቱን እንዲለማመዱናየንግግር ችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ ተደርጓል ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 25 (41.6%) የሆኑ ተማሪዎች አንድ አንድ ጊዜ ያደርጋሉ፣ 17 (28.3%) የሆኑ ተማሪዎች አልፎ አልፎ ያደርጋሉ፣ 8 (13.3%) የሆኑ ተማሪዎች ሁል ጊዜ ያደርጋሉ፣ 5 (8.3%) የሆኑ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋሉ፣ 5 (8.3%) የሆኑት ተማሪዎች ደግሞ በፍጹም አያደርጉም በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው ብዙ መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በሚተገብሩበት ጊዜ ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና እንዲያጎለብቱ ውይይት፣ ክርክርና ጭውውቶችን እንዲያከናውኑ ሢያደርጉዋቸው ጥቂት መምህራን ግን በፍጹም አያደርጉም፡፡

የንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ መምህራን እንዲተገበር በሚያደርጉበት ወቅት ተማሪዎች ተሳትፎዋቸው እንዲጨምርና በራስ መተማመናቸው እንዲጎለብት ስህተት ሲፈጠር በእርጋታና እነሱን በማያስደነግጥ መልክ እንዲያስተካክሉ ማድረግና ከተቻለም እራሳቸው እርስ በርስ መተራረም እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በመጠይቁ ላይ

እንደተገለጸው ተማሪዎች በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት ስህተት ሲፈጠር ቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስ በርስ እንዲተራረሙ ይደረጋል ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 23 (38.3%) የሆኑት ተማሪዎች አንድ አንድ ጊዜ ያደርጋል፣19 (31.6%) የሆኑት ተማሪዎች ብዙ ጊዜ ያደርጋል፣ 10 (16.6%) የሆኑት ተማሪዎች ሁል ጊዜ ያደርግል፣ 8 (13.3%) የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ብዙ ጊዜ አያደርግም በማለት መልሰዋል፡፡ የህ የሚያመለክተው መምህራኖች የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በሚሰጡበት ጊዜ ስህተት ሲፈጠር በተረጋጋ መንፈስና ተማሪዎችን በሚያበረታታ መንገድ እርማት ሲሰጡና እርስበርስ እንዲተራረሙ ሲያደርጉ ጥቂት መምህራን ግን አላረጉም፡፡

መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ወቅት የተለያዩ መተግበሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የንግግር ትምህርትን ውጤታማነትን ለማመልከት መጣር አለባቸው፡፡ የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ የተለያዩ ስዕሎች፣ ቅረጻቅርጾችና ፎቶግራፎችን በመጠቀም ተማሪዎች ያዩትን የተረዱትን ነገር መናገር እንዲችሉ ማድረግ የመምህራን ተግባር ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተማሪዎች መጠይቁ ላይ መምህሩ የተለያዩ ሥዕሎችን፣ ፎቶ ግራፎችንና ቅርጻ ቅርጾችን በመማሪያ ክፍል ውስጥ አምጥቶ ተማሪዎች እንዲናገሩ በማድረግ ሁኔታ ምን ይመስላል ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 11 (18.3%) የሆኑ ተማሪዎች በጣም ጥሩ ነው፣ 14 (23.3%) የሆኑ ተማሪዎች መካከለኛ ነው፣ 2 (3.3%) የሆኑ ተማሪዎች ከፍተኛ ነው፣ 13 (21.6%) የሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ ነው፣ 20 (33.3%) የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ምንም ጥረት አያደርግም በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው መምህራን የንግግር ትምህርትን ተግባራዊ በሚያደርግበት ጊዜ ስእሎችን፣ ፎቶግራፎችንና ቅርጻ ቅርጾችን ተማሪዎች አይተው እንዲናገሩ በማድረግ ሁኔታ የለም ማለት ይቻላል፡፡ መምህራኖቹ ለዚህ አይነት የማስተማር ሁኔታ ትኩረት አይሰጡም፡፡

በአጠቃላይ መምህራን የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ በተግባር በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልና ስህተታቸውን እንዲተራረሙ በማድረግ ሂደት ሙሉ በሙሉ ባይሆንም የተሻለ ትግራ ነው፡፡ በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት ክርክር፣ ውይይትና ጭውውት ተማሪዎች እንዲያደርጉ በማድረግ ደግሞ መምህራኖች ላይ ያለማስተግበር ችግር በተወስነ ሁኔታ ይታያል፡፡ የተለያዩ ፎቶግራፎችን፣ ስእሎችንና ቅርጻ ቅርጾችን አቅርቦ እንዲናገሩ በማድረግ ረገድ ደግሞ የልተሰራበትና ተግባራዊ ያለተደረገ መሆኑን ከመጠይቁ የተገኘ መረጃ ያመለክታል፡፡

### 4.1.3. ከቃለ መጠይቅ የተገኘ የንግግር ክሂል አተገባበር የመምህራን ምላሽ

*4.1.3.1. የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ አቀራረብን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ትንተና*

ጥያቄ ቁጥር. 1. የንግግር ትምህርት ከመቅረቡ በፊት ለተማሪዎች አላማው ግልጽ ያደርጉላቸዋል?

የንግግር ክሂል ትምህርትን መምህራን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት የትምህርቱን አላማ ግልጽ ማድረግ አለባቸው፡፡ ይህን መሰረት በማድረግ ከቃለ መጠይቁ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው መምህራን የንግግር ትምህረት ከመቅረቡ በፊት ለተማሪዎች አላማውን ግልጽ ያደርጉላቸዋል? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 2 (100%) በጣም ከፍተኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ መምህራን የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚተገበሩበት ወቅት አላማን ግልጽ ማድረግ ለንግግር ትምህርትን ከግብ ለማድረስ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ከዚህ መጠይቅም ያገኘነው መልስም እሄንኑ የሚያሳይ ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 2. የንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ ከመደረጉ በፊት ተማሪዎችን ያነቃቃሉ?

በቃለ መጠይቁ ላይ መምህራን እንደገለጹትየንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ ከመደረጉ በፊት ተማሪዎችን ያነቃቃሉ ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ 1 (50) መምህር ከፍተኛ ነው ብሎ ሲመልስ፣ 1 (50) መምህር ደግሞ በጣም ከፍተኛ ነው በማለት መልሶዋል፡፡ እንደሚታወቀው ተማሪዎች የንግግር ትምህርትን በክፍል ውስጥ በሚተገበሩበት ወቅት ለተማሪዎች ማነቃቅያ ማድረግ ተማሪዎች ለትምህርቱ ትልቅ ትኩረት እንዲሰጡና ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ በመጠይቁ መልስ ላይ ለመመልከት እንደ ተቻለው ብዙ ጊዜ የማነቃቃት ስራ እንደሚሰራና ጥሩ ተሞክሮ እንዳለ እንረዳለን፡፡

ጥያቄ ቁጥር 3. ተማሪዎች ስለ ንግግር አቀራረብ እንዲያውቁ አድርጓቸዋል?

መምህራን የንግግር ክሂል ተግባርን በሚያስተምሩበት ጊዜ ተማሪዎች ስለ ንግግር አቀራረብ እንዲያውቁ ማስቻል አለባቸው፡፡ ስለ ንግግር አቀራረብ ተማሪዎች አወቁ ማለት የንግግር ክሂል ተግባርን በሚገባ ለማከናወን አይቸግራቸውም ማለት ነው፡፡ በመጠይቁ ላይ መምህራን ተማሪዎች ስለ ንግግር አቀራረብ እንዲያውቁ አድርገዋል? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ 2 (100%) መምህራን ከፍተኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው የንግግር ክሂል ትምህርት በሚተገበሩበት ወቅት መምህራን የንግግር አቀራረብን ተማሪዎች እንዲያውቁ ተደርጓል ማለት ነው፡፡

ጥያቄ ቁጥር 4. ለንግግር ትምህርት የሚሆኑ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ያስተምራሉ?

የንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ በሚተገበሩበት ወቅት መምህራን መርጃ መሳሪያዎችን መጠቀም ተማሪዎች የተማሩትን ነገር የበለጠ እንዲገነዘቡት ያደርጋቸዋል፡፡በንግግር ክሂል ትምህርት ጊዜ መርጃ መሳሪያ መጠቀም ተማሪዎች ንግግርን በሚገባ ማድረግ እንዲችሉ ያስችላቸዋል፡፡ ይህን መሰረት በማድግ መምህራን በመጠይቁ ለንግግር ትምህርትየሚሆኑ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ያስተምራሉ? ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 1 (50%) መምህር ዝቅተኛ ነው፣ 1 (50%) መመህር ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ ማለት መምህራኑ የንግግር ክሂል

ትምህርትን በክፍል ውስጥ በሚተገበሩበት ወቅት የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን እንደማይጠቀሙ ከመጠይቁ የተገኘው ምላሽ ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ በንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ጊዜ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው አላማን መግለጽ ና ስለ ንግግር አቀራረብ እንዲያውቁ በማድረግ ሁኔታ ላይ ተግባራዊ ያደረጉት ሲሆን፤ ተማሪዎችን በማነቃቃት ሂደት ላይ ደግሞ የተወስነ ጉድለት አለብን በማለት ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ግን መርጃ መሣሪያዎችን በመጠቀም በኩል በመምህራኖች በኩል ያልተጠቀሙት እንደሆነ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

*4.1.3.2. የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ልምምድን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ትንተና*

ጥያቄ ቁጥር 5. በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የህይወት ገጠመኛቸውን እንዲያቀርቡና እንዲለማመዱ ያደርጋሉ?

ከመምህ ራን ቃለ መጠይቅ እንደምንረዳው የንግግር ክሂል ትምህርትን በመማር ማስተማር ሂደት ላይ መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የህይወት ገጠመኞቻቸውን እንዲያቀርቡና እንዲለማመዱ ያደርጋሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 1 (50%) መምህር ዝቅተኛ ነው፣ 1 (50%) መምህር ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚያደርጉበት ወቅት ተማሪዎች የህይወት ገጠመኞቻቸውን እንዲያቀርቡና እንዲለማመዱበት አላደረጉም፡፡

ጥያቄ ቁጥር 6. ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ እንዲለማመዱና ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ያደርጋሉ?

የንግግር ክሂል ትምህርትን መምህራን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ተማሪዎች በሚገባቸውና በተረዱት መንገድ ንግግርን እንዲለማመዱና ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽ እንዲችሉ ማድረግ የመምህራን ከፍተኛ ሚና ነው፡፡ ተማሪዎችም የንግግር ትምህርትን እንደሁኔታዎችና እንደተረዱት ሆኔታ ልምምድ ማድረግና ሁሳባቸውን በነጻነት መግለጽ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በመነሳት በቃለ መጠይቁ መምህራን ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ እንዲለማመዱና ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ያደርጋሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 1 (50%) መምህር ከፍተኛ ነው፣ 1 (50%) መምህር ደግሞ በጣም ከፍተኛ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ ደግሞ መምህራን የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ጊዜ ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ እንዲለማመዱና ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ መደረጉን መረዳት ይቻላል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 7. የሚፈሩና ሀሳባቸውን ለመግለጽ የሚቸገሩ ተማሪዎችን ያበረታታሉ?

መምህራን የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ጊዜ የተለያዩ ባህሪ ያላቸውን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሊያጋጥማቸው ይችላል፡፡ እነዚህ ተማሪዎችም በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ጥንቃቄ ካልተደረገባቸው በሚገባ ለሁሉም እኩል የሆነ ትምህርት ሊደርሳቸው አይችልም፡፡ ስለዚህ መምህራንም የተለያዩ ባህሪያት ያላቸው የመፍራት፣ ሀሳባቸውን ለመግለጽ የሚቸገሩና ሌሎችም ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎቹ በውስጣቸው ፍረሀት እንዳይኖር፣ የሚፈሩ ከሆነም ፍረሀታቸውን ማስወገድ እንዳለባቸውና ሀሳባቸውን ያለምንም ጭንቀት መግለጽ እንዲችሉ ማድረግ የመምህራን ተግባር ነው፡፡ በቃለ መጠይቁም መምህራን የሚፈሩና ሀሳባቸውን ለመግለጽ የሚቸገሩ ተማሪዎችን ያበረታታሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ 1 (50%) መመህር በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ 1 (50%) መምህር ከፍተኛ ነው በማለት መለስ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያስረዳው በንግግር ክሂል ትምህርት ጊዜ መምህራን ጥቂት ጉድለት ቢኖራቸውም በብዛት የመፍራትና ሀሳብን ለመግለጽ የሚቸገሩ ተማሪዎችን እንደሚያበረታቱ ከመጠይቁ የተገኘው መልስ ያስረዳል፡፡

ጥየቄ ቁጥር 8. የንግግር ክሂል ትምህርትን ከሌሎች የክሂል አይነቶች ጋር በማቀናጀት ያስተምራሉ?

የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱን በሚተገብሩበት ጊዜ ተማረዎች ግንዛቤያቸው እንዲጨምር እና እንዲጎለብት ከሌሎች የክሂል አይነቶች ጋር በማቀናጀት ማስተማር ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህ የንግግር ክሂል በምናስተምርበት ጊዜ ሌሎች የክሂል አይነቶችንም በውህደት ማስተማር ያስፈለገው ሁሉም የቋንቋ ክሂሎች ተያያዥነት ስላላቸው ነው፡፡ በመጠይቁ ውስጥ መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን ከሌሎች የክሂል አይነቶች ጋር በማቀናጀት ያስተምራሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ 1 (50%) መምህር ከፍተኛ ነው፣ 1 (50%)መምህር ደግሞ መካከለኛ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከዘህ መልስ የምንረዳው መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርትን በሚተገብሩበት ወቅት ከሌሎች የክሂል አይነቶች ጋር በመቀናጀት ያስተማሩ ቢሆንም በተወሰነ ሁኔታ አንድ መምህር ብዙም እንደማይ ተገበር የገኘው ምለሽ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 9. ተማሪዎች በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ ያደርጋሉ?

የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ችሎታቸውን ለማሳደግ በክፍል ውስጥ የተለያዩ ክንውኖችን በቡድንና በጥንድ እንዲያከናውኑ ማድረግ የመምህር ተግባር ነው፡፡ ተማሪዎች በቡድንና በጥንድ እንዲ ወያዩ ያደርጋሉ? ተብለው መምህራን ሲጠየቁ 1 (50%)

መምህር ከፍተኛ ነው፣ 1 (50%) መምህር መካከለኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ የሚያመለክተው በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት መምህራን የንግግር ተግባርን ተማሪዎች እንዲተገብሩ ሲያደርጉ የጥንድና የቡድን ውይይትን እንዲያከናውኑ አንድ መምህር የሚያደርግ መሆኑን

ሲገልጽ ሌላኛው መምህር ደግሞ ብዙ ጊዜ እንደማይተገብረው ከተገኘው የመጠይቁ መልስ መረዳት ይቻላል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 10. ስዕሎች፣ ፎቶ ግራፎች እና ቅርጻ ቅርጾችን በመስጠት ልምምድ እንዲያደርጉ እና ንግግር እንዲያደርጉ ያደርጋሉ?

የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ውስጥ በምንተገብርበት ጊዜ የተማሪዎችን የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚታዩ ነገሮችን ስዕሎችን፣ ፎቶ ግራፎችንና ቅረጾችን በመጠቀም የመማር ማስተማር ሂደቱን መምህራን ውጤታማ ማድረግ ይችላሉ፡፡በመጠይቁ ላይ መምህራን ስእሎችን፣ ፎቶ ግራፎችንና ቅርጻ ቅርጾችን በመስጠት ልምምድ እንዲያደርጉ እና ንግግርን እንዲያከናውኑ ያደረጋሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ 2 (100%) ሁለቱም መምህራን በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ ሁለቱም መምህራን በንግግር ትምህርት ጊዜ የሚታዩ ነገሮችን በመስጠት ተማሪዎች የንግግር ልምምድ እንዲያደርጉ አለማድረጋቸውን ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡

ጥያቄ ቁጥር 11. ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ከሰዎችና ከመዛግብት ሀሳብ በመሰብሰብ ንግግር እንዲያደርጉ ያደርጋሉ?

ተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርትን በክፍል ከመማር ማስተማር ሂደት ከመምህራቸው ውጪ ከሌሎች ሰዎችና ከመዛግብትም የገኛሉ፡፡ መምህራንም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርትን እንዲተገብሩ በሚያደርጉበት ወቅት ከሰዎችና ከመዛግብቶች የተለያዩ ሀሳቦችን በመሰብሰብ በክፍል ውስጥ በንግግር መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ መምህራን በቃለ መጠይቁ ላይ ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ከሰዎችና ከመዛግብት ሀሳብ በመሰብሰብ ንግግር እንዲያደርጉ ያደርጋሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ 1 (50%) መምህር መካከለኛ ነው፣ 1 (50%)መምህር ደግሞ ዝቅተኛ ነው በማለት መለስ ሰጥተዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው አንዱ መምህር በጥቅቱም ቢሆን ለመተግበር ሲሞከር አንደኛው ግን ያለተገበረ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በአጠቃላይ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በንግግር ክሂል ተምህርት ልማማድ ወቅት መምህራን ተማሪዎች እንዲተገብሩ ያደረጉትሀሳብን በነጻነት መግለጽ፣ የሚፈሩ ተማሪዎችን ማበረታታትን በሚገባ ተማሪዎች እንዲተገብሩት ተደርገዋል፡፡ በንግግር ክሂል ተምህርት ጊዜ ተማሪዎች በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ፣ ከክፍል ውጪ ከሰዎችና ከመዛግብት ሀሳብን ሰብስቦ ማቅረብና የንግግር ክሂልን ከሌሎች የንግግር ክሂል ጋር አቀናጅቶ ማስተማርን በተወሰነ መልኩ ለመተግበር የሞከሩ ሲሆን፤ የህይወት ገጠመኛቸውን እንዲያቀርቡ ማድረግና የሚታዩ ነገሮችን አቅረቦ ተማሪዎች እንዲያቀርቡ ማድረግ ከነ ጭራሹ ያለተሰራ ተግባር መሆኑን ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

*4.1.3.3. የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ሀሳብን በነጻነት መግለጽን በተመለከተ ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘ ትንተና*

ጥያቄ ቁጥር 12.የንግግር ትምህርት በሚማሩበት ወቅት ተማሪዎች የተግባር ስራ ሲሰሩ በመሀል እርምት ይሰጣሉ?

በንግግር ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት የተማሪዎች ስራ የንግግር ተግባሩን መተግበር ወይም መስራት ነው፡፡ ተማሪዎች የንግግር ስራ በሚሰሩበት ወቅት ደግሞ መምህራን ተማሪዎችን በማያሸማቅቅና የጥፋተኝነት እንዳይሰማቸው በሚያደርግ መልኩ የሚሰሩት ነገር ላይ እርምት መስጠት ተገቢ ነው፡፡ በመጠይቁም መምህራን የንግግር ትምህርት በሚማሩበት ወቅት ተማሪዎች የተግባር ስራ ሲሰሩ በመሀል እርምት ይሰጣሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 2 (100%) መምህራን በጣም ከፍተኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ይህ የሚነግረን መምህራን የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ጊዜ ተማሪዎች የንግግር ተግባር ላይ ሲሳሳቱ እርምት እንደሚሰጡ ከቃለመጠይቁ የተገኘው መልስ ይገልጻል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 13. ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስ በርሳቸው መተራረም እንዲችሉ ያደርጋሉ?

በዚህ የንግግር ክሂል ትምህርት ጊዜ ተማሪዎች የተለያዩ የንግግር ተግባራትን በሚተገብሩበት ጊዜ ስህተቶችን ሊፈጽሙይችላሉ፡፡ እነዚህን በንግግር ትምህርት ጊዜ የሚፈጸሙ ስህተቶች መምህራን እራሳቸው ስህተቱን ከማስተካከል

ባሻገር ተማሪዎች እራሳቸው እንዲተራረሙና እርስ በርስ እውቀት መለዋወጥ እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስ በርሳቸው መተራረም እንዲችሉ ያደርጋሉ? ተብለው መምህራን ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 1 (50%) መምህር ከፍተኛ ነው፣ 1 (50%) መምህር ደግሞ መካከለኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው የንግግር ክሂል ተግባር በሚተገብርበት ጊዜ አንዱ መምህር ተማሪዎች ስህተትን እንዲተራረሙ በማድረግ በኩል የተሻ ሲሆን አንድ መምህር ደግሞ በተወሰነ ሁኔታ አልፎ አልፎም ቢሆን ለመትግበር እንደሚሞክር ከቃለ መጠይቁ የተገኘው ምላሽ ያመለክታል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 14. ለማሪዎች በስህተታቸው እንዳይደነግጡ እና ስህተት አንድ የመማሪያ መንገድ እንደ ሆነ ያስረዷቸዋ?

የንግግር ክሂል ትምህርት በሚተገበርበት ወቅት መምህራን ለተማሪዎች በስህተታቸው እንዳይደነግጡና ስህተት አንድ የመማርያ መንገድ እንደ ሆነ ያስረዷቸዋል? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 1 (50%) መምህር ከፍተኛ ነው፣ 1 (50%) መምህር ደግሞ በጣም ከፍተኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ይህ ማለት መምህራኑ የንግግር ክሂል ትምህርትን በሚያስተምሩበት ወቅት ተማሪዎች ስህተት ሲፈጠር መማሪያ መንገድ መሆኑን በተሻለ መንገድ እንደሚነግሯቸው ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ ያስረዳናል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 15. የንግግር ክሂል ትምህርት ከመጠቃለሉ በፊት ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ያበረታታሉ?

መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ወቅት ተማሪዎች ያልገባቸውን ነገርና አስፈላጊ የሆነውን እውቀት እንዲያካብቱ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ ማድረግ የመመህር ተግባር ነው፡፡ ተማሪዎችም የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደትያልገባቸውንና ጥያቄ የሆነባቸው ነገር ካለ አስፈላጊውን እውቀት እንዲይዙ መጠየቅ ይኖርባቸዋል፡፡ በመጠይቁም ውስጥ መምህራን የንግግር ክሂልትምህርት ከመጠቃለሉ በፊት ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ያበረታታሉ? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 2 (100%) መምህራን በጣም ከፍተኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው በንግግር ክሂል ትምህርት ጊዜ ሁለቱም መምህራን ተማሪዎች ከተማሩት ትምህርት ውስጥ ያልገባቸውና ግልጽ ያልሆነ ነገር ካለ እንዲጠይቁ በማድረግ እንደሚያበረታቷቸውከቃለ መጠይቁ መልስ መረዳት ይቻላል፡፡

ጥያቄ ቁጥር 16. በተሰጠው የንግግር ትምህርት ላይ ማጠናከሪያ ሀሳባ ይሰጧቸዋል?

የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ማጠናከሪያ መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ተማሪዎች የንግግር ትምህርትን በሚማሩበት ጊዜ የተመሩት ትምህርት ይበልጥ እንዲገባቸውና የተሻለ እውቀት እንዲኖራቸው መምህራን ማጠናከሪያ ሊሰጧቸው ይገባል፡፡ ተማሪዎች በንግግር ትምህርት ወቅት ማጠናከሪያ የሚሰጣቸው ከሆነ ለትምህርቱም የሚሰጣቸው ፍላጎት ይጨምራል፤ የተሻለ እውቀትም በትምህርቱ ላይ ያካብታሉ፡፡ በመጠይቁ ላይም መምህራን በተሰጠው የንግግር ትምህርት ላይ ማጠናከሪያ ሀሳብ ይሰጧቸዋል? ተብለው ሲጠየቁ የሰጡት መልስ 2 (100%) መምህራን በጣም ከፍተኛ ነው በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት ሁለቱም መምህራን የንግግር ትምህርት ሲያስተምሩ ማጠናከሪያ ለተማሪዎቻቸው በሚገባ እንደሚሰጡ ከቃለ መጠይቁ ላይ ያገኘነው መረጃ ያሳየናል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከተው በሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የተገኘውን መረጃ ስንመለከት የተሰጡት ምላሾች ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይው በስተቀረ በምልከታና በቃለ መጠይቅ የተገኙት ብዙም ልዩነት አይታይባቸውም፡፡ በክፍል ምልከታ ወቅት የንግግር ተግባርን ለማከናወን የቡድን ውይይት ና ክርክሮችን በሚያከናውበት ጊዜ በተለየ ሁኔታ የታየው ነገር የተከራካሪዎች ፍረሀትና መጨናነቅ እንዲሁም ከሚወያዩበት ርዕስ ውጪ መውጣትና የተመልካቾች ስረአት አለመያዝ ተይቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሚወያዩትና የሚከራከሩት ተማሪዎች በቂ ዝግጅት እንዳላደረጉና ሀሳባቸውን በሚገባ አቀናጅተው መናገር እንደማይችሉ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡ ይህም የሚያሳየን ተማሪዎቹ በቂ የዝግጅት ጊዜ እንዳላገኙና ልምምድ እንዳላደረጉ ያስረዳናል፡፡

## 4.2. የመረጃዎቹ ትንተና እና ማብራሪያ

### 4.2.1. የንግግር ክሂል ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶችና ክንውኖች

ከጥናቱ የተገኘውን መረጃ እንደሚያመለክተው በመማር ማስተማሩ ሂደት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያሉ ምዕራፎች የንግግር ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ መልመጃዎችና የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች በውስጡ ተካተዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የንግግር ትምህርትን ለማስተማርና በክፍል ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ትኩረት ተሰጥቶት የተሰራበት

መሆኑን የሚያመክት ነው። መረጃዎቹ እንደሚያመለክቱት በመማር ማስተማር ሂደት የቀረቡ የመማሪያ ይዘቶችና የንግግር ተግባሩን ለማከናወን የቀረቡ ክንውኖችን ለማስተማሪያ መሳሪያዎችና መፅሀፍቶችን ብቻ መሰረት ያደረገ ነው። ሆኖም የንግግር ክሂልን በበለጠ ሁኔታ ለማስፋፋትና ውጤቱ አመርቂ እንዲሆን ከተፈለገ የተማሪዎችን ፍላጎትና ከራሳቸው የህይወት ገጠመኝ ጋር በማቆራኘት የሚቀርብ ቢሆን ተማሪዎች ተነሳሽነት እንዲኖራቸውና በፍላጎት እንዲማሩ ያስችላቸዋል። የንግግር ክሂል ተግባራትን በክፍል ውስጥ በሚተገበሩት ወቅት በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶችና ተግባራት ብቻ የመናገር ችሎታን፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ችሎታና የተግባቦትን ለመፍጠር አነስተኛ እንደሆነ አጥኚው በመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች በሰበሰባቸው መረጃዎች ማወቅ ችሎዋል።

### 4.2.2. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ትግበራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የቋንቋ ክሂሎችን በሚገባ መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርታቸው ውስጥ በሚገባ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች በአግባቡ መጠቀም ከቻሉ የቋንቋ ትምህርታቸውን እውቀት በተገቢው መንገድ ማካበት ወይም ማሳደግ ችለዋል ማለት ነው፡፡ ከነዚህ አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ውስጥ ደግሞ ከላይ በጥናቱ ውስጥ እንደተመለከትነው አንዱ የንግግር ክሂል ነው፡፡ የንግግር ክሂል በተለያዩ ሁኔታዎችና ማህበራዊ ክንውኖች ውስጥ ሀሳባችንን ለመግለጽ ስለምንጠቀምበት በክፍል ውስጥም በመማር ማስተማር ሂደት ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራበት ይገባል፡፡ ስለሆነም በንግግር ክሂል ትምህርረት የመማር ማስተማር ስልትና የተምህርቱ መልመጃዎች የንግግሩን አቀራረብ፣ ልምምድና የተማሪዎችን ተሳትፎ ያካተተና እነዚህ ተግባራት ስራ ላይ በሚያውል መንገድ ተደራጅቶና ተቀናጅቶ መቅረብ አለበት፡፡ የንግግር ክሂል ትምህርትን በማስተማር ሂደት ውስጥ መምህሩ ወደ ትምህርቱ ከመግባቱ በፊት የተማሪዎቹን የትኩረት አቅጣጫ ለመሳብና ለትምህርቱ ፍላጎት እንዲኖራቸው ለማድረግ የማነቃቃት ተግባር ማከናወን ይኖርበታል፡፡ የማነቃቃት ስራ መስራት የሚያስፈልግበት ሁኔታ ቋንቋውን ተጠቅመው ሀሳባቸውን ለመግለጽ ብቻ ሳይሆን ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ለመገንዘብና ፍላጎት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ መምህራን የማነቃቃት ስራ ትምህርትን ለመጀመር ብቻ ሳይሆን የመማር ማስተማር ሂደቱንም ውጤታማ ለማድረግ ይጠቅማቸዋል፡፡ ሆኖም በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ የተገኘውን መረጃ ስንመለከት በተወሰነ ሁኔታ የተሰራበት ቢመስልም ግን ብዙም ትኩረት ተሰጥቶበት እየተሰራበት አይደለም፡፡

ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ መስተጋብርን ተግባራዊ ለማድረግ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት ተሳትፎ የተማሪዎችን በራስ መተማመናቸውን በመጨመር የላቸውን ማህበራዊ መስተጋብር እንዲያሳድጉ ያስችላቸዋል፡፡ ተሳትፎ የተማሪዎችን በራስ መተማመን ብቻ ሳይሆን የእውቀት ደረጃቸውን እንዲጨምሩ ያደርጋል፡፡ መምህራንም በመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎችን ተሳትፎ እንዲጨምር ማድረግ ለትምህረቱ ውጤት አስፈላጊ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታና ከመጠይቆቹ በተገኘ መረጃ የተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎዋቸው ያልተሰራበት፤ ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ እንደሆነና መምህራኖች የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመጨመር ያደረጉት ጥረት አነስተኛ እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱ ውስጥ የንግግር ትምህርትን ተማሪዎች እንዲለማመዱ የተለያዩ ክንወኖችን እንዲተግሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የንግግር ልምምድን በሚያደርጉበት ወቅት ተማሪዎች የግል፣ የቡድንና የጥንድ ድርጊቶችን በክፎል ውስጥ እንዲያከናውኑ ማድረግ ና መምህራን ድረዲቱን ወይም ክንውኑን በመከታተል የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃቸውን ማሳደግ ተገቢ ነው፡፡ እነዚህ ክንውኖችም ውይይት፣ ክርክርና ጭውውት በልምምድ ሰአት የሚሰሩ ከሆነ ተማሪዎች እርስ በርስ የእውቀት ልውውጥና የንግግር ችሎታቸውን እንዲሆም ያላቸውን የአእምሮ ብስለት ይጨምርላቸዋል፡፡ በምልከታ የተገኘው መረጃ ግን መምህራኑ የንግግር ትምህረት ወቅት በልምምድ ጊዜ የጥንድና የቡድን ስራዎችን ጭውውት፣ ክርክርና ውይይት ተማሪዎችን ለማሰራት ብዙም ትኩረት ተሰጥቶት እንዳልተሰራበት የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች እርስ በርሳቸው የሀሳብ ልውውጥ፣ እንዲከራከሩና የሀሳብ መረዳዳት እንዳልነበር ከመረጃው መረዳት ይቻላል፡፡

ተማሪዎች በተለያዩ ማህበራዊ መስተግር ውስጥ ቋንቋን ተጠቅመው ሁሳባቸው በግልጽ ለመናገርና በማህበራዊጉዳዮች ላይ ተሳትፈው ሀሳብን ለመስጠት ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ መምህራንም የተማሪዎችን በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፈው ተቀባይነት ያለው ንግግር ለማድረግ ወይም መስተጋብራዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው አመልካቾች የሆኑ ተግባራትንና የተለያዩ ስእሎችን፣ ፎቶግራፎችንና ቅርጸ ቅረጾችን በክፍል ውስጥ በሚማሩበት ጊዜ በማቅረብ ተማሪዎች እየተመለከቱ ሀሳብ እንዲሰጡና በራስ መተማመናቸው እንዲጨምር እንዲሁም ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽ እንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

በምልከታው ላይ እንደተገለጸው መምህራን ከላይ የተጠቀሱትን ተግባራት በክፍል ውስጥ በማቅረብ ተማሪዎች ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ያላደረጉ መሆናቸውን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በምልከታ፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተገኙት መረተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ መስተጋብርን ተግባራዊ ለማድረግ ተሳትፎ አስፈላጊ ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት ተሳትፎ የተማሪዎችን በራስ መተማመናቸውን በመጨመር የላቸውን ማህበራዊ መስተጋብር እንዲያሳድጉ ያስችላቸዋል፡፡ ተሳትፎ የተማሪዎችን በራስ

መተማመን ብቻ ሳይሆን የእውቀት ደረጃቸውን እንዲጨምሩ ያደርጋል፡፡ መምህራንም በመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎችን ተሳትፎ እንዲጨምር ማድረግ ለትምህረቱ ውጤት አስፈላጊ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታና ከመጠይቆቹ በተገኘ መረጃ የተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎዋቸው ያልተሰራበት፣ ትኩረት ያልተሰጠው ጉዳይ እንደሆነና መምህራኖች የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመጨመር ያደረጉት ጥረት አነስተኛ እንደሆነ መረጃው ያመለክታል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳብ

### 5.1.ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሰሜን ሸዋ ዞን በኩዩ ወረዳ የብሪቲ ሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበርን የተመለከተ ነው። የተፈለገውን አላማ ደግሞ ከግብ ለማድረስ በጥናቱ የቀረቡ ንድፈ ሀሳቦችን በመጠቀም ለመተንተን ሞክሯል። አጥኚውም በብሪቲ ሁለተኛና መሰናዶ ትምህርት ቤት ሁለት መምህራኖችን በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተጠቅሞ የወሰደ ሲሆን፤ ከትምህርት ቤቱ ውስጥ ባሉት የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ ስልሳ ተማሪዎችን በተራ ዕጣ ናሙና አመራረጥ በመጠቀም መርጧል። መረጃዎችንም ለማሰባሰብ የተጠቀመባቸው የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች ምልከታ ፣ የፅሁፍ መጠይቅና የቃል መጠይቅ ናቸው። በመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች የተገኙ የተለያዩ መረጃዎችን በመጠናዊና አይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎች በመጠቀም የጥናቱን ውጤት ለማግኘት ተሞክሯል።

### 5.2. መደምደምያ

በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ተማሪዎች የንግግር ችሎታና ውጤት ላይ ከሚኖረው ጫና በመነሳት በየወቅቱ ከሚነሱ ሀሳቦች፣ ጥናትና ምርምር ና ግኝቶች አብሮ ሊሄድና ሊሻሻል ይገባል። በተለያዩ ምክንያቶች ከሚደረገው የትምህርት ስረአት ፣ የማስተማር ፍልስፍና ና ከሚዘጋጁት ማስተማሪያ መሳሪያዎች ጋር የመምህራን ስልጠና ትኩረት ቢሰጠው በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ ትልቅ ተፅኖ አለው።

የመማር ማስተማር ሂደት ላይ የትምህርቱን አላማ ከሚፈለገው ግብ እንዲያመጣ ለማድረግ በየጊዜው የተለያዩ ጥናትና ምርምሮች እንዲከናወኑ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን በመማር ማስተማር ውስጥ ተማሪዎች በአስፈላጊው መንገድና እውቀታቸውን ሊጨምር በሚችል ሁኔታ እንዲሁም ችሎታቸውን ለማካበት በሚያስችላቸው መንገድ ሁሉም መምህራን ጥረት ማድረግ አለባቸው። መምህራን አመቺ የመማር ማስተማር ሁኔታ በክፍል ውስጥ እንዲኖር ካልተደረገ፣ ለትምህርቱ ትኩረት ተሰጥቶ ማስተማር ካልተቻለ፣ ከተማሪዎች ከዕለት ገጠመኞቻቸውና ከማህበራዊ መስተጋብራቸው ጋር የሚገናኙ ርዕሶችን በማቅረብ የሚያስተምሩ ካልሆነ በተማሪዎቹ ላይ ትምህርቱን የመጥላትና የግዴለሽነት ባህሪ መታየቱ አይቀሬ ነው። በጥናቱ መረጃ ላይ እንደ ተመለከትነው ብዙዎቹ ክንውኖች በመምህራን የማስተማር ፈጠራ ላይ የተመሰረቱ ሳይሆኑ በመማሪያ መፅሀፍ ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ የተማሪዎችን ተሳትፎ በግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው።

የንግግር ክሂል መምህራን በክፍል ውስጥ በሚያከናውኑበት ወቅት የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ አላማዎች ይዘቶችና ክንውኖች እንዲሁም የማስተማሪያ ዘዴዎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ የተማሪዎችን የመናገር ክሂል የሚጨምሩና የተማሪዎችን የመናገር ችሎታ ለማሳደግ አይነተኛ መንገድ የሆኑ መሆን አለባቸው።

መምህራን የመማር ማስተማር ሂደቱን ሊያጠናክርላቸው የሚችል ስልጠና ማግኘት አለመቻላቸውና በክፍል ውስጥ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ሊያነሳሱ የሚችሉ ተግባራትን ባለማከናወናቸው በተማሪዎች መካከል ያለው ተግባቦታዊ መስተብር ፣ የመወያየት ፣ እውቀት የመለዋወጥና በሀሳብ የመተጋገዝ ፎላጎት አናሳ ሆኖዋል። በንግግር ትምህርት ወቅትም ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን ሀሳብን የመለዋወጥና የእውቀት ሽግግር እንዲኖር እንዲሁም እርስ በርስ ስህተትን የመተራረምና ሀሳብን በነፃነት መግለፅ በስፋት በክፍል ውስጥ አልታየም።

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያሳየው በክፍል ውስጥ የቀረቡት የማስተማሪያ ስልቶችና የማስተማር ሂደቶች የተማሪዎቹን የመናገር ችሎታቸውን የሚያዳብሩ ናቸው። ይህም ማለት የቀረቡት የማስተማሪያ ስልቶችና የመምህሩ የማስተማር ሂደት የተማሪዎችን የእርስ በርስ መስተጋብር ተግባቦቶችን ሊፈጥሩ የሚችሉና የተማሪዎችን ተሳትፎ በሚገባ የሚያበረታታ አይደለም። በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት የሚቀርቡ ተግባራት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ነፃ ሆነው ተግባሩን እንዲያከናውኑ የሚያደርግና ችሎታቸውን ለማዳበር በየጊዜው መምህራን ልምምድ እንዲያደርጉ አለማስቻላቸውን አጥኚው ባገኘው መረጃ መረዳት ችሏል።

## 5.3. የመፍትሄ ሀሳብ

የጥናቱ መነሻ ሀሳብ የሆነው የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ የታዩ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ የመፍትሄ ሀሳቦችን መጠቆሙ አስፈላጊ ነው። ሆኖም በጥናቱ ላይ ከተነሱት ጥያቄዎችና የተገኙ ውጤቶችን መነሻ በማድረግ የተለያዩ የመፍትሄ ሀሳቦችን ለማቅረብ ተሞክሯል።

- የንግግር ክሂል ተግባራትን መምህራን በክፍል ውስጥ በሚያቀርቡበት ጊዜ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት፣ ገጠመኞች፣ ማህበራዊ መስተጋብሮችን መሰረት አድርጎ ቢቀርብ፤
- መምህራን የንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት የንግግር ተግባሩ ከመቅረቡ በፊት የትምህርቱን አላማ ለተማሪዎች ግልፅ ቢያደርጉ፤
- መምህራን የንግግር ክሂል ተግባርን ተማሪዎች እንዲያከናውኑ ከማድረጋቸው በፊት ተማሪዎችን ሊያነቃቁ የሚችሉ ተግባራትን ቢያከናውኑ፤
- የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚተገብሩበት ወቅት ተማሪዎችን የመናገር ችሎታ ሊያሳድጉ የሚችሉ ተግባራትን እንዲለማመዱ ቢደረግ፤
- መምህራን የንግግር ክሂል ተግባራትን በሚተገብሩበት ወቅት ከተማሪዎች የህይወት ተሞክሮ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች ወደክፍል ውስጥ አምጥቶ እንዲማሩበት ቢያደርጉ፤
- በንግግር ትምህርት ጊዜ ለመናገር የማይደፍሩና የመፍራት ችግር ያለባቸውን ተማሪዎችን ትኩረት በመስጠት እንዲለማመዱ ቢደረግ፤
- በንግግር ክሂል ትምህርት ተግባር ወቅት የመናገር ችሎታ ያላቸውና ለመናገር የሚደፍሩ ብቻ መሳተፍ ሳይሆን ሁሉንም ተማሪዎች ተግባሩን እንዲያከናውኑ ማድረግ እንዲሁም የመምህር ተኮር የመማር ማስተማር ስልት ሳይሆን ተማሪ ተኮር የትምህርት አቀራረብን የመማር ማስተማር ሂደትን ተግባራዊ ቢያደርጉ፤
- የተማሪዎቹን የንግግር ክሂል ተግባር ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራትን ፦የተማሪዎችን እድሜ፣ ፆታ፣ የእውቀት ደረጃ፣ የአካባቢ ባህል፣ ማህበራዊ አኗኗርና ቋንቋን ያገናዘበ እንዲሆኑ በሚዘጋጁበት ወቅት የፍላጎት ደሰሳ ቢደረግ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራበት፣
- የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ወቅት መምህራን አዳዲስ ሀሳቦችን ከማስተማሪያ ዘዴዎች ጋር ለማቀናጀት በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላት የተለያዩ ስልጠናዎችን ለመምህራን በማዘጋጀት ቢሞክሩ፤
- በንግግር ልምምድ ወቅት ተማሪዎች እርስ በርስ የወወያየት ባህል እንዲኖራቸው ቢደረግ።
- ተማሪዎች በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት የንግግር ተግባራትን በቀላሉና በነፃነት ሀሳባቸውን መግለፅ በሚችሉበት ሁኔታ ቢከወን፤
- መምህራን በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት የንግግር መተግበሪያዎችን ስዕሎችን፣ ፎቶ ግራፎችንና ቅርፃ ቅርፆችን በክፍል ውስጥ በማቅረብ ተማሪዎች በማየት ንግግር እንዲያቀርቡ ቢደረግ፤
- በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ብዛት የንግግር ክሂልን ለመተግበርና ተማሪዎች ትምህርቱን በምቾት እንዳይማሩ ስለሚያደርጋቸው የሚመለከታቸው አካላት የመማሪያ ክፍሎችን ሁኔታ በማየት ተጨማሪ ክፍሎችን ቢሰሩና ሁኔታዎችን በማመቻቸት የመማር ማስተማር ሂደቱ

# ዋቢመጽሐፍት


ማረውአለሙ፡፡(1998)፡፡**የአማርኛቋንቋማስተማሪያዘዴ**፡፡አዱስአበባ ፤ብርሃንናሠላምማተሚያቤት፡፡

በድሉዋቅጅራ፡፡ (2007)፡፡**በስነ-ፅሐፍቋንቋማስተማር**፡፡ፊርኢስትትሬዲንግ ኀላ.የተ.ማ

ተስፋዬሸዋዬ፡፡ (1981)፡፡**‹‹ስነ-ልሳንእናየቋንቋማስተማር››**፡፡የቋንቋዎችእና ጥናትተቋም፣አዲስአበባ፣ዩኒቨርስቲ፡፡ (ያልታተመ)

አብረሀም ገ/ዮሐንስ፡፡ (2003)፡፡ **የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ዉስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና የትምህርቱ አቀራረብ**፡፡የኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ፡፡

እጅጉይማም፡፡ (2003) ፡፡‹‹**በደብረ ብረሃን ከተማ በተመረጡ ሶስት መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሰባተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የመናገር ክሂል አቀራረግምገማ**››፡፡ የአርትስ ማስተር ዲግሪ ማሟያ፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፡፡

Alumettu,T.(2018).**Developing the Students English Speaking abilities Through.**

Annsnow, Marguerite. (1991). “**Teaching language through content**” In Marine Celce- Murcia (editors). Teaching English as asecon or forein language. Boston; Heile and Heinle New burty hous. (pp 315-325)

Benter, O.(2015). **Theaching speaking skills in English language using class room activities in secondary school level in Eldoret municipality**. Kenia.Jornal of Education and practice. Vol-6 No.35

Bygate.M. (1987) .**speaking** .oxford university press.

Byme, D. (1976). **Teaching oral English London**.Longman.

Brown &Yule .(1983). <<**A Holistic approach toTeaching speakinin the langage class room**>> (symposium) g

Broum Fate .(1984).**Imprving for class room**.Interaction.London longman.Group UK limited.

Byrne.D.(1987).**Techinque in Class room Interaction**.Students Englewood Cliffs:M.printice Hail.

Celce,M.& Olshtain,E.(2000).**Discourse and Context in Language Teaching.** AGuidef or LanguageTeachers.Cambridge.CambridgeUniversity Press.

Dedi, Rahaman Nur.(2017).**Techniques for Teaching Speaking**. inWidya Gama Mahakama University. Vol.2No.1.PP 1-13

Echeverria Ellen W. (1987).**Speaking on Issues** ; An introduction to public communication. New york: Harcourt brace and campany.

Florez , C. and A. Marry (1999). **Improving Adult English Language, Learners Speaking Skill.** New York: National center for ESL Litracy Education.

Grant, Neville. (1987). **Making the most of your text book**. London: Longm

Harmer, J. (2001). **The practice of English Language Teaching**. (3rd ed). Malysia: Longman.

Harmer .J. (2007).**How to teach English**. Llondon.longman

Kumari, Av.(2014). **Methods of Teaching English**.Gunture: New Era Publications.

Mc Donough, J. and Christopher, Shaw (1994).**Material and methods in ELT**: ATeacher Guide. Oxford: Black well.

Rechards .jack.(1994).**the context of language teaching**.Cambridge. cumbridge university press.

Widdowson H.G(1992).**Teaching Language as communication**.Oxford University Pres

# አባሪዎች

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል ትምህርት የክፍል ዉስጥ አተገባበር

በክፍል ዉስጥ የንግግር ትምህርት በሚከናወንበት ጊዜ በምልከታ የምንከታተልበት ቅጽ

ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ዞን-----------------ወረዳ---------

የትምህርት ቤቱ ስም--------------------

ምልከታዉ የተካሄደበት የክፍል ደረጃ-----------------

ምልከታዉ የተደረገበት ቀን-----------------------

ምልከታው የተደረገበት ክፍለ ጊዜ----------------

ምልከታው የተደረገበት ሰአት-----------------------

በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው የትምህርት ርዕስ--------------

ይህ የምልከታ ቅጽ የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል ተግባራት የክፍል ውስጥ አቀራረብን ለመከታተል ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ የምልከታ ተግባርን በክፍል ውስጥ በምን ተገብርበት የሚከተሉትን መመሪያዎች መከተል አለብን፡፡ መመሪያዎቹም ተግባራቱ የተከናወኑ ከሆነ (√) ምልክት ''አዎ'' ከሚለው ላይ ይደረጋል፡፡ ተግባራቱ ተግባራቱ ያልተከናወኑ ከሆነ ደግሞ (×) ምልክት ''አይደለም'' ከሚለው ላይ ይደረጋል፡፡

| ተ.ቁ | የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ጥያቄዎች | አዎ | አይደለም |
|---|---|---|---|
| 1 | የትምህርቱ አላማ ለተማሪዎች በግልጽ ቀርቧል? | | |
| 2 | ትምህርቱ ሲቀርብ የመማሪያ መጽሀፍትን መሰረት ያደረገ ነው? | | |
| 3 | የትምህርቱ አቀራረብ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን መሰረት ያደረገ ነው? | | |
| 4 | የትምህርቱ የአቀራረብ ሂደት ተማሪዎችን ያሳተፈ ነው? | | |
| 5 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃቸውን ያማከለ ነው? | | |
| 6 | ተማሪዎች የንግግር ትምህረትን እንድለማመዱ ይበረታታሉ? | | |
| 7 | የቀረቡት የትምህረት መመሪያዎች ለተማሪዎች ግልጽ ናቸው? | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 8 | በልምምድ ጊዜ ተማሪዎች በደንብ ይሳተፋሉ? | | |
| 9 | ንግግርን ለመለማመድ የተሰጣቸውን ጊዜ በአግባቡ ተጠቅመዋል? | | |
| 10 | የንግግር ክሂል ማጎልበቻ ተግባራትን (ክርክር፣ ውይይት፣ ጭውውትና ሌሎች) አከናውነዋል? | | |
| 11 | የንግግር ልምምድን በግልና በቡድን አከናውነዋል? | | |
| 12 | የንግግር ክሂልን የማስተማር ሂደቱ ሁሉንም ተማሪዎች ያሳተፈ ነው? | | |
| 13 | የመፍራትና የመናገር ልምድ የሌላቸው ተማሪዎች እንዲበረታቱ ተደርጓል? | | |
| 14 | በንግግር ልምምድ ወቅት ሁሉም ተማሪዎች ተግባሩን እንዲያከናውኑ ተደርጓል? | | |
| 15 | በሚለማመዱበት ወቅት ተማሪዎች እርስበርስ የመወያየት ባህል እንዲኖራቸው ይደረግ ነበር? | | |
| 16 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎች ሲሳሳቱ እርምት ለመስጠት ጥረት ተደርጓል? | | |
| 17 | የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉና በነጻነት የሚችሉበት ሁኔታ የተከናወኑ ናቸው? | | |
| 18 | ስዕሎችንና ፎቶግራፎችን ክፍል ውስጥ በማቅረብ በንግግር መልክ ዕንዲያቀርቡ ተደርጓል? | | |

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና ኮምንኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነ-ፅሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የፅሁፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች የዚህ መጠይቅ ወና አላማ የአማርኛ ቋንቋ  ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት ችግሮች ካሉ የመፍትሄ ሀሳብ ለመፈለግና ለተጀመረው ጥናታዊ ፅሁፍ ተጨማሪና ማጠናከሪያ ሐሳብ ለማግኘት እንዲሁም መረጃ ለመሰብሰብ ነው። ከተዘጋጀው መጠይቅ የሚገኘው ውጤት ለተጀመረው ጥናታዊ ፅሁፍ ስኬታማነት ትልቅ እገዛ ስለሚኖረው ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ትክክለኛ መረጃ መሰብሰብ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ የቀረቡትን ጥያቄዎች ትኩረት ሰጥታችሁ በማንበብ ትክክል ነው ብላችሁ የምትገምቱትን መልስ እንድትሰጡንና መጠይቁን በመሙላት ለምታደርጉልኝ ትብብር ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው።

ክፍል አንድ:- ቀጥሎ ለቀረቡት ክፍል ቦታዎች ትክክለኛውን መረጃ በመሙላት እንድትተባበሩኝ በአክብሮት እጠይቃለው።

-ትምህርት ቤቱ የሚገኝበት ዞን------------- ወረዳ-------

-የትምህርት ቤቱ ስም --------------------------------

-የተማሪው የክፍል ደረጃ-----------------------------

-ፆታ        ወንድ----------     ሴት----------

-እድሜ------------------------------

-የአፍ መፍቻ ቋንቋ ---------------------------------

ክፍል ሁለት:- የሚከተሉትን ጥያቄዎች የሚያመላክቱትን ሆሄያት በማክበብ ትክክለኛውን

መልስ ምረጡ።

1.የንግግር ትምህርትን ተግባራዊ ከማድረጋችሁ በፊት አላማው በግልፅ ይነግራችኋል?

ሀ.ብዙ ጊዜ ይነገረናል። ለ.አልፎ አልፎ ይነገረናል። ሐ.አንድ አንዴ ይነገረናል።

መ.በፍፁም አይነገረንም።

2.በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የንግግር ትምህርት ወቅት የመከታተል ፍላጎት አለህ/ሽ?

ሀ.ከፍተኛ ነው። ለ.በጣም ከፍተኛ ነው። ሐ.መካከለኛ ነው። መ.ዝቅተኛ ነው። ፍላጎት የለኝም።

3.የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት መምህራን ማነቃቅያዎችን ያቀርባሉ?

ሀ.ብዙ ጊዜ ያነቃቃሉ። ለ.አንድ አንድ ጊዜ ያነቃቃሉ። ሐ.አልፎ አልፎ ያነቃቃሉ።

መ.ምንም አያነቃቁም።

4.የአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የንግግር ክሂል መተግበሪያ ክፍሎች የንግግር ክሂልን

ለማዳበር ይጠቅማሉ?

ሀ.በጣም ይጠቅማሉ። ለ.በመጠኑም ቢሆን ይጠቅማል። ሐ.አይጠቅምም መ.ሌላ ካለ----------------

5.በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት ምን ያህል ተሳትፎ ታደርጊያለሽ/ህ?

ሀ.ብዙ ጊዜ እሳተፋለው። ለ.መምህሩ ሲጠይቀኝ ብቻ እሳተፋለው። ሐ.አልፎ አልፎ

እሳተፋለው። መ.ተሳትፎ የለኝም።

6.መምህሩ የንግግር ክሂል ተግባር ከመጀመሩ/ሯ በፊት አጠር ያለ መመሪያ ይሰጣሉ?

ሀ.አንድ አንዴ ይሰጣሉ። ለ.ብዙ ጊዜ ይሰጣሉ። ሐ.በፍፁም አይሰጡም። መ.መመሪያቸው

ግልፅ አይደለም።

7.ተማሪዎች የንግግር ተግባር ከማከናወናቸው በፊት ምሳሌ ይሰጧችኋል?

ሀ.አንድ አንዴ ይሰጣሉ። ለ.አልፎ አልፎ ይሰጣሉ። ሐ.ብዙ ጊዜ ይሰጣሉ። መ.በፍፁም

አይሰጡም።

8.መምህሩ የንግግር ክሂል ትምህርትን በሚተገብሩበት ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች እኩል

የመሳተፍ እድል ይሰጣሉ?

ሀ.ብዙ ጊዜ ይሰጣሉ። ለ.አንድ አንድ ጊዜ ይሰጣሉ። ሐ.ሁል ጊዜ ይሰጣሉ። መ.በፍፁም

አይሰጡም።

9.በግልና በቡድን  ውይይትና ክርክር በአንድነት በመሆን የንግግር ክሂልን የመተግበር

ሁኔታ በክፍል ውስጥ ነበር?

ሀ.አንድ አንድ ጊዜ አለ። ለ.አልፎ አልፎ አለ። ሐ.ብዙ ጊዜ አለ። መ.ምንም የለም።

10.በግልና በቡድን የንግግር ክሂል ተግባር በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ወቅት መምህሩ

እየተከታተሉ ያበረታታሉ?

ሀ.አንድ አንዴ ያበረታታሉ። ለ.አልፎ አልፎ ያበረታታሉ። ሐ.ብዙ ጊዜ ያበረታታሉ።

መ.ምንም አያበረታቱም።

11.ለመናገር የሚፈሩ ተማሪዎችን በራስ መተማመን እንዲኖራቸው የማበረታታት ሂደቱ

እንዴት ያለ ነው?

ሀ.በጣም ጥሩ ነው። ለ.በጣም ከፍተኛ ነው። ሐ.መካከለኛ ነው። መ.ዝቅተኛ ነው።

12.የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ ለመተግበር የክፍሉ ሁኔታ እንዴት ያለ ነው?

ሀ.ምቹ ሁኔታ አለው። ለ.በመጠኑ ምቹ ነው። ሐ.በጣም ምቹ ነው። መ.ምቹ አይደለም።

13.የንግግር ተግባርን በምታከናውኑበት ጊዜ ሀሳባችሁን በነፃነት እንድትገልፁ መምህሩ ያደርጓችኋል?

ሀ.በጣም ጥሩ ነው። ለ.በጣም ከፍተኛ ነው። ሐ.መካከለኛ ነው። መ.ዝቅተኛ ነው።

14.በክፍል ውስጥ በጭውውት፣ በክርክርና ውይይት መልክ ተግባራቱን እንዲለማመዱና የንግግር ችሎታን እንዲያጎለብቱ ተደርጓል?

ሀ.አንድ አንድ ጊዜ ያደርጋሉ። ለ.አልፎ አልፎ ያደርጋሉ። ሐ.ሁል ጊዜ ያደርጋሉ። መ. አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋሉ። ሠ.በፍፁም አያደርጉም።

15.በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት ስህተት ሲፈጠር ቀጥታ ከመናገር ይልቅ እርስ በርስ እንዲተራረሙ ይደረጋል?

ሀ.አንድ አንድ ጊዜ ይደረጋል። ለ.ብዙ ጊዜ ይደረጋል። ሐ.ሁል ጊዜ ይደረጋል። መ.ብዙ ጊዜ አይደረግም።

16.መምህሩ የተለያዩ ሥዕሎችን፣ ፎቶ ግራፎችንና ቅርፃ ቅርፆችን በመማሪያ ክፍል ውስጥ አምጥቶ ተማሪዎች እንዲናገሩ በማድረግ ሁኔታ ምን ይመስላል?

ሀ.በጣም ጥሩ ነው። ለ.መካከለኛ ነው። ሐ.ከፍተኛ ነው። መ.ዝቅተኛ ነው። ሠ.ምንም ጥረት አያደርግም።

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ የቋንቋዎች ጥናት የጆርናሊዝምና የኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋነቋ ስነ-ጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

የአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አተገባበር

ለአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረቡ የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች

የተከበሩ የ--------------ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህር ይሄ ቃለ መጠይቅ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂል አተገባበር በክፍል ውስጥ እንዴት እንደሚ ተገብሩ ለማወቅ የተዘገጀ ነው፡፡ ከመጠይቁ የሚገኘው መልስ ለሚጠናው ጥናት ከፍተኛ አገዛ ስለሚኖረው እርሶም ኢሄንኑ ተረድተው ጥናቱ የታለመለት ግብ እንዲመታ ቃለመጠይቁን ላይ በመሳተፍ ሙያዊ እገዛ እነዲያደርጉልኝ በትህትና እጠይቃለው፡፡በመቀጠልም ውድ ጊዜዎን ሰውተው ስለሚተባበሩኝ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ክፍል አንድ፡-የመምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መረጃ

1. የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ስም----------------
2. ጾታ-----------
3. ዕድሜ------------
4. የትምህርት ደረጃ--------------
5. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ----------------
6. የአገልግሎት ዘመን------------------

ክፍል ሁለት፡-የንግግር ክሂል ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን መሰረት ያደረጉ የቃለ

መጠይቅ ጥያቄዎች

ከዚህ በመቀጠል ለቀረቡት የቃለ መጠይቅ ጥያቄዎች አምስት አማራጮች ቀርበዋል፡፡ከነዚህ አማራጮች ውስጥ ለእረሶ መለስ ነው ብለው የሚያስቡትን አንድ አማራጭ በቃል ይመልሳሉ፡፡

| ተ.ቁ | ለቃለ መጠይቁ የቀረቡ ጥያቄዎች | ከፍተኛ | ዝቅተኛ | መካከለኛ | በጣም ከፍተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የንግግር ትምህርት ከማቅረቡ በፊት ለተማሪወች አላማውን ግልጽ ያደርጉላቸወል? | | | | | |
| 2 | የንግግር ክሂል ተግባርን በክፍል ውስጥ ከመደረጉ በፊት ተማሪዎችን ያነቃቃሉ? | | | | | |
| 3 | ተማሪዎች ስለ ንግግር አቀራረብ እንዲያውቁ አድረገዋል? | | | | | |
| 4 | ለንግግር ትምህርት የሚሆኑ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ያስተምራሉ? | | | | | |
| 5 | በክፍል ዉስጥ ተማሪዎች የህይወት ገጠመኛቸውን እንዲያቀርቡና እንዲለማመዱ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 6 | ተማሪዎች በራሳቸው መንገድ እንዲለማመዱና ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 7 | የሚፈሩና ሀሳባቸውን ለመግለጽ የሚቸገሩ ተማሪዎችን ያበረታታሉ? | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | የንግግር ክሂል ትምህርትን ከሌሎች የክሂል አይነቶች ጋር በማቀናጀት ያስተምራሉ ? | | | | | |
| 9 | ተማሪዎች በቡድንና በጥንድ እንዲወያዩ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 1 0 | ስዕሎች፣ ፎቶ ግራፎችን እና ቅርጻቅርጾችን በመስጠት ፈዎዎድ እንዲያደርጉና ንግግር እንዲያደርጉ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 1 1 | ተማሪዎች ከክፍል ውጪ ከሰዎችና ከመዛግብት ሀሳብ በመሰብሰብ ንግግር እንዲያደርጉ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 1 2 | የንግግር ትምህርት በሚማሩበት ወቅት ተማሪዎች የተግባር ስራ ሲሰሩ በመሀል እርምት ይሰጣሉ? | | | | | |
| 1 3 | ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስ በርሳቸው መተራረም እንዲችሉ ያደርጋሉ? | | | | | |
| 1 4 | ለተማሪዎች በስህተታቸው እንዳይ ደነግጡና ስህተት አንድ የመማሪያ መንገድ እንደሆነ ያስረዷቸዋል? | | | | | |
| 1 5 | የንግግር ክሂል ትምህርት ከመጠቃለሉ በፊት ተማሪዎች ያልገባቸውን እንዲጠይቁ ያበረታታሉ? | | | | | |
| 1 6 | በተሰጠው የንግግር ትምርት ላይ ማጠናከሪያ ሀሳብ ይሰጧቸዋል? | | | | | |

# bBebriti 2gna dereja mesenado temehrt bet afachewen beoromigna yefetu ye10gna kefel temariwoch beamarigna quanqua yemenager kihil yekefel weset ategebaber (□□□□ 2□ □□□ □□□□ □□□□□ □□ □□□□□ □□□□□ □□□ □1

ORIGINALITY REPORT

| 10% | 9% | 0% | 3% |
|---|---|---|---|
| SIMILARITY INDEX | INTERNET SOURCES | PUBLICATIONS | STUDENT PAPERS |

PRIMARY SOURCES

| | | |
|---|---|---|
| 1 | etd.aau.edu.et<br>Internet Source | 5% |
| 2 | repository.ju.edu.et<br>Internet Source | 3% |
| 3 | Submitted to Addis Ababa University<br>Student Paper | 1% |
| 4 | etd.dbu.edu.et<br>Internet Source | <1% |
| 5 | hvlopen.brage.unit.no<br>Internet Source | <1% |
| 6 | repository.radenintan.ac.id<br>Internet Source | <1% |
| 7 | calidad.uniovi.es<br>Internet Source | <1% |
| 8 | www.cla.purdue.edu<br>Internet Source | <1% |

| | | |
|---|---|---|
| 9 | www.aictda.gov.et<br>Internet Source | <1 % |
| 10 | archer.chnu.edu.ua<br>Internet Source | <1 % |
| 11 | ir.bdu.edu.et<br>Internet Source | <1 % |

| | | | |
|---|---|---|---|
| Exclude quotes | Off | Exclude matches | Off |
| Exclude bibliography | Off | | |